
EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 8

## ስለ ዳይኖሰሮችና ቅሪት አካሎች በተመለከተ

PK3



AppleTree

# ክፍል 8


## ስለ ዳይኖሰሮችና ቅሪት አካሎች በተመለከተ

©2021
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከዚህ በታች በቅጂ መብት የተያዙትን መብቶች ሳይገድብ ፣ የትኛውም የዚህ ህትመት ክፍል  እንደገና ሊባዛ ፣ ሊከማች ወይም ወደ ሌላ የማስመለሻ ስርዓት ሊተላለፍ አይችልም  ፣ ወይም በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ ፣ ሜካኒካል ፣  ፎቶ ኮፒ ማድረግ ፣ መቅዳት ወይም በሌላ መንገድ) ያለ ቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ።

AppleTree Institute for Education Innovation
1801 Mississippi Ave SE, 3rd Floor
Washington, DC 20020

የቅጂ መብት © 2021 ጽሑፍ እና ስዕሎች። AppleTree Institute(አፕል ትሪ ኢንስቲትዩት) መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# PK3 ክፍል 8 ምልከታ



## ክፍል 8 ቃላት

- መበስበስ
- ዳይኖሰር
- የጠፋ
- ስሜቶች
- ቅሪቶች
- የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ
- ያለፈ ጊዜ

**ውድ ቤተሰቦች፡**

ወደ ክፍል 8 እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 8 ስር ልጅዎ ስለ ዳይኖሰሮች እና ነገሮች በጊዜ ሂደት እንዴት እንደሚቀየሩ በተመለከተ ይማራል።

## ክፍል 8 መጻህፍት




- *The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል/ዘ ሊትል ቢትል* በ Felicia R. Truong
- *I Love Dinosaurs/ አይ ላቭ ዳይኖሰርስ* በ AppleTree Institute for Education Innovation
- *I Can Count Lots of Ways!አይ ካን ካውንት ሎጽ ኦፍ ዌይስ* በ Lydia Carlis
- *A Reef Tale/ኤ ሪፍ ቴል* በ Felicia R. Truong
-

*በተጨማሪም፣ ለሁሉም መጻህፍት ቀድመው የተቀዱ ንባቦች ለአዋቂዎች ጠቃሚ ምክሮች /Tips for Adults፣ ዳይኖሰሮች እና ቅሪት አካላት በሚለው ስር በሚገኘው Sparkler መተግበሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል።*


***የ ECR በቤት ውስጥ የሚሰሩ ተግባሮች/ECR @ Home Activities ዳይኖሰሮችና የሱፍ ክምር መስራትን፣ ስለ አፈር መማርን፣ የዛፍ የህይወት ኡደትን እና ስለ ዳይኖሰሮች እና ቅሪት አካሎች የሚያጠኑ ተመራማሪዎችን ያጠቃልላሉ። ልጅዎ እስከ 10 የሚደርሱ ነገሮችን ይቆጥራል፣ ከ3-5 ቁጥሮች ስሞችን ይጠራል፣ የአቅጣጫ ቃላትን በመጠቀም ይለማመዳል፣ የድምጽ ቀለሞችን ይለያል፣ እንዲሁም ባለ ሁለት ደረጃ መመሪያዎችን ይከተላል። ልጅዎ በተጨማሪም ስለ ስሜቶች፣ ጓደኝነት እና ችግሮችን ማስወገድ ይማራል። ይህን ትምህርት ከልጅዎ ጋር እንደ የትህትና ቃላትን መጠቀም ወይም ክፉ ከመሆን ይልቅ መሸሽ የመሳሰሉ ስለ ችግር አፈታት የተመለከቱ ሁሉንም የልጅዎን ስዕሎች በማስገባት የችግር አፈታት መጽሀፍ በማዘጋጀት ማስፋፋት ይችላሉ። መጽሀፉን ልጅዎ ችግር ወይም ፈታኝ ነገር ሲያጋጥመው እንዲጠቀምበት በቀላሉ ማግኘት በሚችልበት ቦታ ያስቀምጡለት።***


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 1


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# በተፈጥሮ ውስጥ የሚፈጠሩ ለውጦች



## በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

ስለ ዛፍ የህይወት ዑደት በመማር እና ሁለታችሁም ቀደም ሲል እና አሁን ምን እንደምትመስሉ በማነጻጸር ነገሮች በጊዜ ሂደት ውስጥ እንዴት እንደሚቀየሩ ይማራል። ይህ ዳይኖሰሮች እጅግ ከረጅም ጊዜ በፊት ይኖሩ እንደነበር እንዲገነዘብ ይረዳዋል። ልጅዎ በተጨማሪም የድምጽ ቀለሞችን ይለያል፣ ስለ ስሜቶች ይናገራል እንዲሁም እስከ 10 የሚደርሱ ቁሶችን ይቆጥራል። እነዚህን ተግባሮች በዙሪያዎ የሚፈጠሩ ለውጦችን ለይተው በማሳየት ማስፋት ይችላሉ፣ ለምሳሌ፡ በመንደርዎ ውስጥ የሚገኙ ዛፎች እንዴት ከወቅቶች ጋር እንደሚቀየሩ፣ የህንጻ ቀለም እንዴት በጊዜ ሂደት እየለቀቀ እንደሚሄድ ወይም ቀደም ሲል መራመድ የማይችል ህጻን ዘመድዎ እንዴት አሁን መራመድ እንደቻለ።

## ቁልፍ ቃላት



### መበስበስ

በተፈጥሮ ሂደስ ቀስ በቀስ በጊዜ ሂደት ፈራርሶ መጥፋት



### ያለፈ ጊዜ

ከዚህ በፊት የተፈጠረ ነገር


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ልክ እርስዎ እያደጉ ሲመጡ እንደተቀየሩት ሁሉ ነገሮች እንዴት እንደሚቀየሩ ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ህጻን እያሉ ማድረግ ስለማይችሉት ሆኖም አሁን ማድረግ ስለሚችሉት ስለሆነ ነገር ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## STEM: ስንት ጣቶች አሉ?

- 7 ጣቶችዎን ወደ ላይ ያድርጉ እና ልጅዎን ወደ ላይ ያደረግኩት ስንት ጣቶች ነው? ብለው ይጠይቁት። ለልጅዎ ጣቶችዎን እንዲቆጥር ይፍቀዱለት። ከዚያም ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው የእጅ ጣቶቹን ወደ ላይ እንዲያደርግ ያድርጉ።
- ይህን ተግባር ከ0 (መጀመሪያ የእርስዎን ያሳዩ) እስከ 10 መካከል ባሉት ቁጥሮች ከ3-4 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ።
- ቁጥር ለመቁጠር ጣቶችን መጠቀም ለልጅዎ በኋላ ላይ ለሂሳብ ስሌቶችና የችግር አፈታት ይረዳዋል።

## በግል መማር: የለውጦች ምልከታ ክፍል 1

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ አበቦች፣ ቅጠሎች ወይም የተቀለመ ቁራጭ ወረቀት፣ ወረቀት፣ ከለሮች፣ *በአማራጭነት ወረቀት እኩሌታ ላይ ይጠፉና በእያንዳንዱ እኩሌታ ላይ ‹‹በፊት›› እና ‹‹በኋላ›› ብለው ይጻፉ***

- ለልጅዎ **ነገሮች እንዴት በጊዜ ሂደት እንደሚቀየሩ እየተማርን ነው። እስኪ በዚህ አበባ ምርምር እንስራ** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ላይ አንድ ላይ ሆነው በአበባው ላይ ምን እንዳየ - ምን እንደሚመስል፣ ምን ስሜት እና ምን አይነት ሽታ እንዳለው ይነጋገሩ።
- ለልጅዎ **ከአበባው ላይ የተመለከትከውን ነገር ልትስል ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን ስለ አበባው በተመለከተ በ‹‹በፊት›› ክፍል ላይ ወይም በሙሉ ወረቀቱ ላይ እንዲጽፍና እንዲስል ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ አበባውን እንተወው እና ያለ ውሀ ከጥቂት ቀናት በኋላ እንዴት እንደሚቀየር እንይ** ይበሉት። ስዕሉን ያስቀምጡት እና አበባውን በቀን 3 በድጋሚ ለመወያየት እንድትችሉ ልጅዎ መመልከት በሚችልበት ቦታ ያስቀምጡት።
- አበቦች ወይም ቅጠሎች ከሌሉዎት የተቀለመ ወረቀት ግማሽ ላይ ቆርጠው ያውጡ። ወረቀቱን ተመልከቱና ተነጋገሩ። አንደኛውን ቁራጭ ከፍተኛ የፀሀይ ብርሀን በሚያገኝበት በታ እና ሌላኛውን ጨለማ ቦታ፡ ምሳ፡ ቁም ሳጥን ወይም ጥቁር ቦርሳ ውስጥ ያስቀምጡ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## እውቀት፡ የድምጽ ቀለሞችን መለያየት


- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን በድምጽ ቀለማቸው እንከፋፍል** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እስኪ beetle የሚለውን ቃል ምቶች እናገናኝ። Bee** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **tle። beetle የሚለው ቃል ስንት ድምጾች አሉት? አዎ፡ 2! Bee-tle፣ bee-tle** ይበሉት።
- ከዚያም **አሁን ደግሞ አንተ ትሞክራለህ። forest** (for-est) **የሚለውን ቃል ምቶች አገናኝ** ብለው ይንገሩት። ሙከራውን little (lit-tle) በሚለው ቃል ደግማችሁ ስሩ።
- ይህ ለልጅዎ ቀላል ተግባር ከሆነ የራሱን ባለ ሁለት ድምጽ ቃላት እንዲያስብ ይጠይቁት ወይም የሚሞክረው ባለ ሶስት ድምጽ ቃል ይስጡት (di-no-saur, skel-e-ton)።

## ያንብቡ፡ *ዘ ሊትል ቢትል*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል*]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *The Little Beetle* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም **በመጀመሪያ ቡ ተናዶ ነበር። በኋላ ግን የእንጨት ቤቱን በማጣቱ ወይም እንጨት ስላለቀበት መስጋት እንደሌለበት ተረዳ። አንተ ቡን ብትሆን ምን ይሰማሀል?** ብለው ይጠይቁት።

የዚህን መጽሀፍ በቅድሚያ የተቀዳ ምንባብ በSpakler መተግበሪያ ላይ በ‹‹ለአዋቂ ሰዎች የተሰጡ ፍንጮች” ክፍል፣ ቅሪት አካሎችና ዳይኖሰሮች ስር ያገኙታል።




**ትንሹ ጥንዚዛ**
ፅሁፍ እና ምስል : ፌሊሲያ አር ትሩንግ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ማክሰኞ



## **STEM:** የዛፍ የህይወት ዑደት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የዛፍ የህይወት ዑደት](), *[The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል]()*, ከለሮች**

- ለልጅዎ **የሀር ትሉ ሹ የሆነ ሰው እንጨቱን እንደበላበት ሰግቷል። እንጨት የተቆረጠ ዛፍ አካል ነው። እስኪ ስለ ዛፍ የህይወት ዑደት እንነጋገር። ዛፎች ልክ እንደ እንስሳት ሁሉ የህይወት ዑደት አላቸው!** ብለው ይንገሩት።
- ዛፎች ከችግኝ አንስቶ እስከ ዛፍነት እንዴት እንደሚያድጉ ለመንገር ስዕሎቹን ይጠቀሙ። ከዚያም ዛፎች ከመድረቃቸውና ሹ መጠቀም ወደሚችለው እነጨትነት ከመቀየራቸው በፊት ወደ ሙሉ ዛፍነት ያድጋሉ። ከዚያም እንጨቱ በስብሶ ቆሻሻ ይሆናል።
- ከዚያም ልጅዎ የህይወት ዑደት ስዕሉን ቀለም ሊቀባ ይችላል።




## በግል መማር፡ የዛፍ መፈግፈጊያዎች ወይም ስዕሎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ የተለያዩ አይነት ቅጠሎች ወይም የዛፍ ቅርፊት**

- ለልጅዎ **የዛፍ ቅጠሎች ወይም ቅርፊቶች ውፍረትን ለማየት መፈተግ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ወረቀቱን እንዴት በቅጠሉ ወይም ቅርፊቱ ላይ እንዴት እንደመሚያስቀምጥ እና በዝግታ ከለሩን እንዴት በወረቀቱ ላይ መፈተግ እንደሚችል ያሳዩት (ወረቀቱን በማንሳት እና የከለሩን ጎን በመጠቀም ቢሆን ይመረጣል)።
- ዛፍ ወይም ቅጠል የማያገኙ ከሆነ ልጅዎ የሚያየውን ዛፍ ስዕል ሊስል ይችላል።
- ከዚያም በሰራው ዲዛይን ላይ ምን እንደሚያይ ተነጋገሩ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 1 ቀን 2

## እውቀት፦ ስሜቶች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ስሜቶች, ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ሁላችንንም በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ስሜቶች ይሰሙናል** ብለው ይንገሩት። ስለተለያዩ ስሜተች ለመነጋገር ስዕሎች ይጠቀሙ። ከ2-3 ስሜቶች ይምረጡ እና እነዚህ ስሜቶች ስለተሰሙዎ ጊዜያት እና እነዚህ ስሜቶች ሲሰሙን ሰውነታችን ምን ስሜት እንደሚሰማው ተነጋገሩ።
- ልጅዎን የሚወደውን ስሜት እንዲመርጥ እና ይህ ስሜት ስለተሰማው ጊዜ እንዲስልና እንዲጽፍ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም ስለ ስዕሉና ስለዛ ስሜት እንዲነግርዎ ይጠይቁትና ይህ ስሜት ስለተሰማዎ ጊዜ ያካፍሉት።
- የስሜቶች ስዕሉን በክፍሉ ውስጥ በሙሉ ለመጠቀም ያስቀምጡት።

### ስሜቶች




## የጆርናል ሙከራ፦ ዛፎች


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የዛፎች የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከዛፎች ስለምትወዷቸው ነገሮች ተነጋገሩ። ዛፎች ለእንስሳቶች መጠለያና ምግብ ሊሆኑ ይችላሉ። ዛፎች እንደ ወረቀትና እንጨት፣ ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶች ሊሆኑ ይችላሉ።
- ልጅዎ ስለ ዛፍ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ከዛፎች ስለምትወደው ነገር ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________


ስለዛም የምትወዱት ምንድን ነው?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 1 ቀን 3

## STEM: የሀር ትል መቁጠር



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የተለያዩ የሀር ትሎች፣](#) ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች**

- ለልጅዎ **በዚህ ገጽ ላይ ስንት የሀር ትሎች እንዳሉ ቁጠር** ብለው ይንገሩት
- **አሁን የሀር ትሎቹን ቀለም መቀባትና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ** ይበሉት። እንደ አስፈላጊነቱ ልጅዎን ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት።
- ከዚያም የተለያየ ብዛት ያላቸው የሀር ትሎችን አንድ ላይ ያድርጉ፣ ምሳ: 2 የሀር ትሎች፣ ከዚያም 7 የሀር ትሎች፣ ቀጥሎም ልጅዎን የሀር ትሎቹን እንዲቆጥራቸው ይጠይቁት።

## በግል መማር: የለውጦች ምልከታ ክፍል 2

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ አበቦች፣ ቅጠሎች ወይም የቀን 1 የተቀለመ ወረቀት፣ የአበቦች/ቅጠሎች/የቀን 1 ወረቀት ስዕሎች፣ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ነገሮች በጊዜ ሂደት እንዴት እንደሚቀየሩ እየተማርን ነው። ከጥቂት ቀናት በፊት አበቦችን ተመልክተን አስቀምጠናቸዋል። እስኪ አሁን ምን እንደመሰሉ እንይ** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር አሁን በአበባው ላይ ምን እንደሚያይ - አበባው ምን እንደሚመስል፣ ምን ስሜት እንዳለውና ምን እንደሚሸት ተነጋገሩ። አበባው ምን ያክል ተቀየረ ወይም በሰበሰ? ብለው ይጠይቁት።
- ከዚያም **አሁን በአበባው ላይ ስለምታየው ነገር ስዕል ልትስልና ልትጽፍ ትችላለህ** ይበሉት። ልጅዎን ስለ አበባው በ ‹‹በኋላ›› ክፍሉ ላይ ወይም በአዲስ ቁራጭ ወረቀት ላይ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥሎም በስዕሎቹ መካከል ስላሉት ልዩነቶች ተነጋገሩ
- በአበባ ምትክ ወረቀት የሚጠቀሙ ከሆነ የጸሀይ ብርሀን እንዲያገኝ በተደረገውና ጨለማ ቦታ በተቀመጠው ወረቀት ቀለም መካከል ያለውን ልዩነት አነጻጽሩ። የጸሀይ ብርሀን ወረቀቱን የበለጠ ቀለሙን እንዲለቅ ማድረግ አለበት።
- *በአማራጭነት - አበባውንe ማስቀመጥ እና ከጥቂት ተጨማሪ ቀናት በኋላ መልሳችሁ ማየት ትችላላችሁ።*


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 1 ቀን 3

## እውቀት፥ ትሁን ምን ስሜት እየተሰማን እንደሆነ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ስሜቶች**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ሁለታችሁም አሁን ምን ስሜት እየተሰማችሁሁ እንደሆነ ተነጋገሩ። ከዚያም **ሁላችንም ስሜቶች አሉን። በተመሳሳይ ጊዜ አንድ አይነት ነገር ብናደርግም እንኳ የተለያዩ ስሜቶች ሊኖሩን ይችላሉ። አሁን ምን ይሰማሀል? እኔ ____. ስሜት ይሰማኛል** ብለው ይንገሩት።
- እነዚያ ስሜቶች ሲሰሟችሁ ሰውነታችሁ ምን ስሜት እንደሚሰማው እና ምን እንደምትመስሉ ተነጋገሩ።
- ልጅዎ ምን ስሜት እንደሚሰማው ሊስልና ሊጽፍ ይችላል።

## ያንብቡ፥ ***The Little Beetle/***ዘ ሊትል ቢትል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *The Little Beetle* ምንባብን ያንብቡ
- ከዚያም **ሹ እያንዳንዱ እንስሳት እንጨቴን እየበሉብኝ ነው ብሎ የሚያስብ በመሆኑ ምክንያት በእያንዳንዱ እንስሳት ይበሳጫል። ሆኖም ሁሉም እንስሳት ‹‹አይደለም›› በማለት እንጨቶቹን እንዳልበሉ አብራርተውለታል** ይበሉት።
- **አንዳንድ ጊዜ ለሆነ ሰው ‹‹አይደለም›› ማለት አለብን። እስኪ ለሆነ ሰው ‹‹አይደለም›› ብለህ መንገር ስለነበረብህ ጊዜ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።




**ትንሹ ጥንዚዛ**
ፅሁፍ እና ምስል : ፌሊሲያ አር ትሩንግ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 1 ቀን 3

## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ባለፈው ምሽት


- ለልጅዎ **እስኪ ጌም እንጫወት! ተንጋለህ ተኛና እንቅልፍ የተኛህ እያስመሰልክ መመሪያዎችን አዳምጥ። መመሪያዎቹን በምታዳምጥበት ወቅት ነቅተህ መመሪያዎቹን መከተል ትችላለህ። በተኛህበት ወቅት የሆነ ሰው የሚዘል ዳይኖሰር እግር ያስቀምጥብሀል! ከእንቅልፍህ ስትነቃ እንደ ትንሹ ዳይኖሰር ትዘላለህ!** ብለው ይንገሩት
- ሌሎች ባለ ሁለት ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት፣ ለምሳሌ፣ የዳይኖሰርህን ጣቶች አሳይና ጭራህን አወዛውዝ።
- ልጅዎ ተግባሩን መምራት እንዲችል ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## በጋራ መማር፥ ያለፈና የአሁን ጊዜያችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ የእርስዎና ልጅዎ የህጻንነታችሁ ፎቶዎች (ካሉ)፣ መስታወት ወይም የእርስዎና ልጅዎ የቅርብ ምስሎች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የየራሳችሁን የህጻንነት ምስሎች ተያዩ። ሁለታችሁም ህጻን ስለነበራችሁበት ጊዜ እና ጊዜ ሲያልፍና እያደጋችሁ ስትመጡ ምን እንደተከሰተ ተነጋገሩ።
- የህጻንነታችሁን ምስሎች አሁን ከምትመስሉት ገጽታ ጋር አነጻጽሩ። ምስሎቹ ከሌሏችሁ ምን ትመስሉ እንደነበር እና በፊት ማድረግ ስለማትችሏቸው ሆኖም አሁን ማድረግ ስለምትችሏቸው ነገሮች መነጋገር ትችላላችሁ። በተጨማሪም ስለራስዎ እርስዎን የሚመስል ወጣት ዘመድዎን በመጥቀስ መግለጽ ይችላሉ።
- ከዚያም **ሁላችንም አናረጃለን። ወደፊት ስናረጅ ምን እንመስላለን ብለህ ታስባለህ? እስኪ በስዕል እንሳለው** ብለው ይንገሩት። የሁለታችሁንም የወደፊት ምስሎች ለመሳል በጋራ ስሩ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 1 ቀን 4

## STEM: ደን መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ የወረቀት ጥቅሎች፣ የእቃ መያዣዎች፣ ማጣበቂያ የመሳሰሉ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ወይም የመጫወቻ ሊጥ ወይም [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ](#)**



በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።


©2020. AppleTree Institute. All Rights Reserved

በመጨዋቻ ሊጥ የምግብ ዝግጅት
(FE)

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከታብሌት ወይም ስልክ ላይ የደን ስዕሎችን ይመልከቱ
- ከልጅዎ ጋር ስለሚያያቸው ዛፎችና እንስሳት ተነጋገሩ። ከዚያም **እስኪ አሁን የራሳችንን ደን እንስራ** ብለው ይንገሩት። አንድ ላይ የራሳችሁን ደን ለመስራት የወረቀት ጥቅሎች ወይም የመጫወቻ ሊጥ ተጠቀሙ።
- ከዚያም በደናችሁ ውስጥ ሊኖሩ ስለሚችሉ የዛፎችና የእንስሳት አይነቶች ተነጋገሩ።

## በግል መማር፡ የቀሻሻ አርት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ ቆሻሻ/አፈር፣ የቡና መሬት ወይም ጨው፣ ወዘተ**





- ለልጅዎ **ሹ የሚመገበው እንጨት ካረጀና ከበሰበሰ በኋላ እንደ ብዙ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ወደ ቆሻሻነት ይቀየራል** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር ስለ ቆሻሻ ምን እንደሚመለከት - ምን ስሜት እንደሚፈጥር፣ ምን እንደሚመስል፣ ምን እንደሚሸት፣ ወዘተ ተነጋገሩ። ልጅዎን በተጨማሪ ስለ ቆሻሻ ምን እንደሚያስብ ይጠይቁት።
- ከዚያም **በዚህ ቆሻሻም ሌላ ቆሻሻ መስራት ትችላለህ! በማጣበቂያ ዲዛይን ስራ። ከዚያም አርትህን ለመስራት በማጣበቂያው ላይ የተወሰነ ተጨማሪ ቀሻሻ ጨምርበት** ይበሉት። ልጅዎን አርቱን እንዲያዘጋጅ ይርዱት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሃሙስ



## እውቀት፥ ዘ ሊትል ቢትልን መልሶ መናገር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል*]

- ለልጅዎ **ይህን መጽሀፍ ትናንትና አንብበናል** ይበሉት።
- ከዚያም **በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለተከሰቱ ስለ ሁለት ነገሮች ልትነግረኝ ትችላለህ? በመጀመሪያ ምን ተከሰተ? ቀጥሎስ ምን ተከሰተ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ ምን እንደተከሰተ እየተናገሩና እየተመለከቱ ባሉበት ወቅት ስዕሎችን ይጠቀሙ። ከዚያም ልጅዎን ስለሚያስታውሳቸው ስለ ሁለት ነገሮች እንዲናገር ይጠይቁት።
- ታሪክ ማስታወስ ለልጅዎ የማስታወስና ታሪክ መልሶ የመናገር ክህሎቶችን እንዲያዳብር ለመርዳት አስፈላጊ ነው።




**ትንሹ ጥንዚዛ**
ፅሁፍ እና ምስል : ፌሊሲያ አር ትሩንግ

## የጆርናል ሙከራ፥ ከረጅም ጊዜ በፊት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ልክ እንደ ዳይኖሰሮች በጣም ከረጅም ጊዜ በፊት መኖር ምን ይመስላል ብሎ እንደሚያስብ ተነጋገሩ።
- ልጅዎን የሚያስበውን ነገር እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ በጣም ከረጅም ጊዜ በፊት መኖር ምን ይመስላል ብለህ እንደምታስብ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


ስም፥ ___________________

ከእጅግ ብዙ አመታት በፊት መኖር ምን ይመስል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ከእጅግ ብዙ አመታት በፊት መኖር ምን ይመስል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አረብ



## STEM: 3-5

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ በትናንሽ የወረቀት ቁርጥራጮች ላይ ከ3-5 ያሉ ቁጥሮችን ይጻፉ። አንድን ቁጥር ሁለት ወረቀቶች ላይ ይጻፉ።**

- አንዱን የቁጥሮች ስብስብ የያዘ ካርድ ለልጅዎ ይስጡ ሌላኛውን ስብስብ ያስቀምጡ።
- ልጅዎን **በቁጥሮች እንጫዎት ይበሉት። ቁጥር የያዘ ካርድ አሳይሃለሁ አንተ ቁጥሩን ትነግረኛለህ በመቀጠል አንተ ላይ ካሉት ካርዶች ውስጥ ቁጥሩን የያዘውን ካርድ አውጥተህ ታሳየኛለህ።**
- ልጅዎ በተራው እርስዎን እንዲጠይቅዎና ካርዱን አውጥተው እንዲያሳዩት ህጉን ይቀይሩት።
- የቁጥሮችን ብዛት በመጨመር ወይም ልጅዎ ዕቃዎችን ከካርዶች ቁጥር ጋር እንዲያዛምድ በማድረግ ጨዋታውን ፈታኝ ማድረግ ይችላሉ።
- የተጠቀማችሁባቸውን ካርዶች ለሌላ ጊዜ ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፡ ቅድመ ታሪክ ዋሻዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ [የድንጋይ ላይ ስዕሎች]፣ ጥቅል ወረቀቶች፣ መያዣዎች፣ ትናንሽ ሳጥኖችና ሌሎችም የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች**



- ስዕሎችን ከልጆችዎ ጋር ይመልከቱ እና **ከብዙ ዓመት በፊት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በህይዎታቸው ውስጥ የሚገጠሟቸውን ዋና ዋና ነገሮች የሚያሳዩት በዋሻ ውስጥ ባሉ ድንጋዮች ላይ ስዕሎችን በመሳል እንደነበረ ይንገሯቸው። ዋሻዎች በተራሮች ወይም ደግሞ በመሬት ላይ ያሉ ቀዳዳዎች መሆናቸውን ያስረዷቸው።**
- **ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ለማሳየት የራስዎን ዋሻና የዋሻ ላይ ስዕሎች መስራት ይችላሉ።**
- ልጆችዎ የራሳቸውን ዋሻና የዋሻ ላይ ስዕሎች እንዲሰሩ ይፍቀዱላቸው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK4 ክፍል 8 ሳምንት 1 ቀን 5

## እውቀት፥ በቃላት ቀለም መዝለል

- **ቃላትን ወደ ቃላት ቀለም በምንከፍልበት ጊዜ በመካከሉ እንዝለል** ይበሏቸው።
- **ቅላጼዎቹን ተከትለን ከማጨብጭብ ይልቅ፣ በመዝለል እንግለጻቸው** ይበሏቸው። **Water የሚለው ቃል ውስጥ ያሉትን ቅላጼዎች ተከትለን እንዝለል Wa**(እናቆማለን) **ter። በ Water ውስጥ ስንት የቃላት ቀለም አሉ? አዎ 2 Wa-ter፣ Wa-ter።**
- **አሁን እናንተ ሞክሩ። Rainbow በሚለው ቃል ውስጥ የቃላት ቀለምን ለዩ።** ( rain-bow)። kitten የሚለውንም እንዲሁ (kit-ten) እንዲሁም puppy(pup-py)።
- ልጆችዎ እርዳታዎን ከፈለጉ ያግዟቸው ገና እየተማሩ ስለሆነ።
- ለልጅዎ አስቸጋሪ ካልሆነ፣ የራሳቸውን ባለ ሁለት ቀለም ቃላት እንዲያስቡ ይጠይቋቸው ወይም ባለ ሶስት ቀለም የሆኑ ቃላትን ይስጧቸውን እና እንዲሞክሩ ያድርጓቸው (ham-burg-er, pine-ap-ple)።

## ያንብቡ፥ ***The Little Beetle/*** *ዘ ሊትል ቢትል*


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [***The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል***]


- ከልጆችዎ ጋር *ዘ ሊትል ቢትል* የሚለውን መጽሃፍ ያንብቡ።
- በመቀጠል **ቡ የግንድ ቁራጩ ጠፍቶ በጣም ተጨንቋል። ሊ የሰጠችው መፍትሄ ምንድን ነው? ቡ ችግር አለመኖሩን እንዲረዳ ሊ ያደረገችበት መንገድ ምንድን ነው?** ብለው ልጅዎን ይጠይቁት።
- **ሊ የእሷን የግንድ ቁራጭ አብረው ተጠቅመው በኋል ሌላ እንፈልጋለን አለችው።**






**ትንሹ ጥንዚዛ**
ፅሁፍ እና ምስል : ፌሊሲያ አር ትሩንግ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።










©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

**የድንጋይ ላይ ስዕሎች (FE)**

# ሳምንት 2


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 8 ሳምንት 2 ምልከታ

## ስለ ዳይኖሰሮችና ቅሪት አካሎች በተመለከተ

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጆችዎ ስለ ዳይኖሰሮች እና ቅሪት አካላት ይማራሉ። የድምጽ ቀለም መለየትን፣ እስከ 10 እቃዎች መቁጠርን፣ ችግር እንዴት እንደሚፈታ ይማራሉ። እንደነዚህን እንቅስቃሴዎች የተወሰኑ ስራዎችን ስትሰሩ ለምሳሌ ቲሸርቶችን በምታጥፉበት ጊዜ መቁጥር፣ ወይም ደግሞ የምትወዷቸውን መዝሙሮች በምትሰሙበት ጊዜ የቃላትን የድምጽ ቀለም በመለየት እነዚህ እንቅስቃሴዎች ማራዘም ትችላላችሁ።



### ቁልፍ ቃላት



**ዳይኖሰር**

በጣም ከብዙ አመታት በፊት ይኖር የነበረና አሁን ግን ከምድረ ገጽ የጠፋ ተሳቢ እንስሳ ነው



**የጠፋ**

ከምድረ ገጽ የጠፋ እና በአሁኑ ግዜ የማይገኝ ተክል ወይም እንስሳ



**ቅሪት አካል**

በድንጋይ ውስጥ ተጠብቀው የተቀመጡ እንስሳት ወይም ዕጽዋት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለ ዳይኖሰርስ እና ቅሪት አካላት ትማራላችሁ። ይህንን ትምህርት ከመጀመራችሁ በፊት ስለምትፈልጉት ዳይኖሰርስ ጻፉና ሳሉት።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 2 ቀን 6


## STEM: 3-5 ባለህበት ቁም ዳንስ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቅት፣ እርሳስ፣ ሙዚቃ፣ ከ3-5 የቁጥር ካርዶች**

- የቁጥር ካርዶችን በወለሉ የተለያዩ ቦታዎች ላይ አስቀምጡ።
- ልጆችዎን፣ **የቁጥር ካርዶችን በመጠቅም ባለህበት ቁም የተሰኘውን ጨዋታ እንጫወታለን** ይበሏቸው። በወለሉ ላይ ያሉ ቁጥሮችን በጋራ ጥሩ።
- ለልጆችዎ፣ **ሙዚቃው ሲጀምር መደነስ ትችላላችሁ። ሙዚቃው ሲያቆም አንድ ቁጥር እጠራለሁ። ቁጥሩን ከወለሉ ላይ ፈልጋችሁ ታገኙና አጠገቡ ትቆማላችሁ።**
- የተወሰኑ ዙሮችን በዚህ መልኩ ተጫወቱ። በመቀጠል ልጆችዎ ጨዋታውን እየመሩ እርስዎ የሚያገኙትን ቁጥር እንዲጠሩ ያድርጉ።

## በግል መማር፡ የዳይኖሰርን በቅርጽ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** **[የዳይኖሰር ቅርጾች/የዳይኖሰርን ቅርጾች](#)**, ከለር፣ ህጻናትን የማይጎዳ መቀስ፣ ***እንደ አማራጭ - ወረቀቶቹን ወደካርድቦርድ ያጣብቋቸው፣ ለምሳሌ የእህል ካርቶኖች***



- ለልጆችዎ **እነዚህን ዕቃዎች በመጠቀም ዳይኖሰር መስራት ትችላላችሁ** ብለው ይንገሯቸው። ሲጨርሱ ስላለቀው ዳይኖሰር ምን እንዳስተዋሉ በጋራ ተነጋገሩ።
- ልጆችዎ ቅርጾችን እንዲቆርጡ ከማገዝዎ በፊት ቀለም እንዲቀቧቸው ይፍቀዱላቸው።
- በመቀጠል ቁርጥራጮችን ገጣጥመው ዳይኖሰር እንዲሰሩ ይፍቀዱላቸው። ቁርጥራጮችን ካለቀው ዳይኖሰር ላይ ማስቀመጥ ይችላሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## እውቀት፥ ችግሮች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ስሜቶች, ወረቅት፣ ከለር**

- አንድን ስሜት ለምሳሌ ንዴት ለልጆችዎ ካሳዩ በኋላ **የሚያናድድ ችግር ገጥሟችሁ ያውቃል?** ብለው ይጠይቋቸው።ስለችግሩ በጋራ ተነጋገሩና ሲናደዱ ምን እንደሚመስሉና ሰውነታችው ምን ስሜት እንደሚሰማው ይጥይቋችው።
- ልጆችዎ ችግሩን ለመፍታት እንዲጽፉና እንዲስሉ ይፍቀዱላቸው፣ ይህን በማድረግዎ ልጆችዎ ሌላ ተጨማሪ ንዴት እንዳይሰማቸው ያደርጋሉ።
- በመቀጠል **ችግሩን ለመፍታት ምን እንዳደረጋችሁ ንገሩኝ** ይበሏቸው። በሚናደዱበት ጊዜ ችግሩን ለመፍታት ሊሰሯቸው የሚችሏቸውን ነገሮች ለምሳሌ በጥልቀት መተንፈስ በጋራ ተነጋገሩ።
- በ Sparkler መተግበሪያ የ "'ጨዋታ" ክፍል ላይ ያሉትን '' የመረጋጋት" እንቅስቃሴዎች ከልሷቸው።

### ስሜቶች





## ያንብቡ፥ ዳይኖሰር እወዳለሁ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *I Love Dinosaurs/ዳይኖሰር እወዳለሁ*


- ከልጆችዎ ጋር *ዳይኖሰር እወዳለሁ* የሚለውን መጽሃፍ አንብቡ።
- በመቀጠል **ትንሿ ልጅ ስለተለያዩ የዳይኖሰር ዓይነቶች አውርታ ነበር። እናንተ የምትወዱት የትኛውን ዳይኖሰር ነው?** ብለው ይጠይቋቸው።

በተጨማሪም፣ ለሁሉም መጻህፍት ቀድመው የተቀዱ ንባቦች ለአዋቂዎች ጠቃሚ ምክሮች /Tips for Adults፣ ዳይኖሰሮች እና ቅሪት አካላት በሚለው ስር በሚገኘው Sparkler መተግበሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል።





አፕልትሪ ኢንስቲትዩት ለትምህርት
ፈጠራ ምስል በ ክርስቲን አካምፒራ
(I Love Dinosaurs)
ዳይኖሰሮችን እወዳለሁ



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## STEM: ቅሪት አካላት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የቅሪት አካላት መፈጠር](), [Fossils](), ከለሮች**




- **ልጆችዎን ስለ ቅሪት አካላት እንማር** ይበሏቸው። **ቅሪት አካላት ድንጋይ ላይ የተቀመጡ የእንስሳት ወይም እጽዋት አካላት ናቸው።** ዳይኖሰርስ እንዴት ቅሪት እንደሆነ ለመነጋገር ቅርጹን ተጠቀሙ።
- ከዛም ሶስት የቅሪት ዓይነት ስዕሎችን ከሳዩዋቸው በኋላ እንዲህ ይበሉ፣ **የተወሰኑ የቅሪት ዓይነቶችን እንመልከት። ቅሪት የሚሰራው አንድ እንስሳ ወይ ዕጽዋት መሬት ላይ ካረፈ በኋል በሚያስቀረው ቦታ ነው። ካስት ደግሞ የሚሰራው አንድ እንስሳ ወይም ዕጽዋት ሲሞትና ጠንካራ እንዲሆን ቦታውን ድንጋይ ሲሸፍነው ነው። አምበር የሚባለው ደግሞ ከዕጽዋት የሚገኝ የሚያጣብቅ ፈሳሽ ነው። ከመድረቁ በፊት እንስሳትንና ዕጽዋትን ወደ ውስጡ ስቦ ሊያስገባ ይችላል።**

## በግል መማር፡ የቅሪት ቅርጾችን መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [ቅሪት አካላት](), የመጫወቻ ሊጥ ወይም [የመጨዋቻ ሊጥ አሰራር](), የሚያስደስቱ አሻራ ያላቸው ነገሮች ለምሳሌ ቅርፊቶች፣ ድንጋዮች፣ ቅጠሎች፣ አሻንጉሊቶች፣ ሹካዎች እና ሌሎችም**




- ከልጆችዎ ጋር የቅሪት ቅርጽ ምስሎችን ተመልከቱ።
- ልጆችዎን **እነዚህን ዕቃዎች የመጫዎቻ ሊጡ ላይ በመጫን እንዚህን ቅሪት አካላት መስራት ትችላላችሁ** ይበሏቸው። **ዕቃዎቹ ከሊጡ ላይ ሲነሱ የሚቀሩት ቦታዎች ቅርጾች ይሆናሉ**። ይህንንም ያሳዩዋቸው።
- ልጆችዎ የራሳቸውን እቃዎች በመጠቀም ቅርጾችን እንዲሰሩ ይፍቀዱላቸው።
- በመቀጠል ስለ ተለያዩ ቅርጾች በጋራ ተነጋገሩ ቅርሶቹ ምን እንደሚመስሉና ምን ስሜት እንደሚሰጡ አወዳድሯቸው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ የቃላት ቀለምን መለየት

- ልጆችዎን **ቃላትን ወደ የቃላት ቀለም እንከፋፍል** ይበሏቸው።
- **በ Fossil ውስጥ ያሉትን የድምጽ ቀለም ስንከፋፍል እናጨብጭብ** ይበሏቸው። Fos (እናቆማለን) sil። ስንት የቃላት ቀለም አሉ? አዎ 2፣ Fos, sil፣ fos-sil::
- **አሁን እናንተ ሞክሩ። በ** amber **ውስጥ ያሉትን የድምጽ ቀለም ስትከፋፍሉ አጨብጭቡ** (am-ber)። puzzle ንም እንዲሁ(puz-zle) ድገሙት።
- ይህ ጨዋታ ለልጆችዎ ከቀለላቸው የራሳቸውን ሁለት የድምጽ ቀለም ያላቸው ቃላት እንዲያስቡ ይጠይቋቸው ወይም ባለ ሶስት የድምጽ ቀለም ቃላት እንዲሞክሩ (di-no-saurs, but-ter-fly) የሚሉትን እርስዎ ይስጧቸው።

## የጆርናል ሙከራ፥ ዳይኖሰር ማየትና ስሜቱ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር፣ እርሳስ፣ ዳይኖሰር ማየት የጆርናል ገጽ፣ ስሜቶች**




- ከልጆችዎ ጋር ዳይኖሰር ቢያዩ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል በጋራ ተወያዩ። አምሯችሁን እንዲያስታውስ ለማድረግ የስሜት ቻርትን በጋራ ተጠቀሙ።
- ልጆችዎ ስለዚህ ጉዳይ ስዕል እንዲስሉ እና እንዲጽፉ ያድርጓቸው።
- በመቀጠል፣ ልጆችዎን **ህይወት ያለው ዳይኖሰር ማየት ምን አይነት ስሜት ሊፈጥር እንደሚችል እስኪ ንግሩኝ** ብለው ይጠይቋቸው። **ምን አይነት ስሜት ይሰማችሁ ነበር? ምን ታደርጉ ነበር?** ብለው ይጠይቋቸው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

በህይወት ያለ ዳይኖሰር ብታዩ ምን ይሰማችኋል?



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 Unit 8 Week 2 Day 8

## STEM: ቲ. ሬክስ መቁጠር


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [T. Rex Sets/ቲ. ሬክስ ስብስቦች](), **ከለር፣ ህጻናትን የማይጎዳ መቀስ**



- ልጆችዎን **በዚህ ገጽ ምን ያህል ትላልቅ ዳይኖሰሮች እንዳሉ ቁጠሩ** ብለው ይንገሯቸው።
- **አሁን ትላልቅ ዳይኖሰሮቹን ቀለም ቀታችሁ ቆርጣችሁ አውጧቸው።** አስፈላጊ ከሆነ ልጆችዎ ቆርጠው እንዲያወጧቸው ያግዟቸው።
- የተለያዩ የT ሬክሶች መጠኖችን ያስቀምጡ። ለምሳሌ 10 T ከዛ 4 T ካወጡ በኋላ ልጆችዎ እንዲቆጥሯቸው ያድርጉ።ቆጥረው ከጨረሱ በኋላ እንዲረዳቸው የመጨርሻውን ድምር ቁጥር እርስዎ ይድገሙላቸው፣ **ለምሳሌ አዎ 10! 10T ሬክስ አላችሁ ይበሏቸው።**

## በግል መማር: የኔ ዳይኖሰር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቅት፣ ከለር ወይም ጠፍጣፋ ቅርጽ ያለው ዉሃማ ቀለም ያለው ሰሌዳ፣** [**ዳይኖሰር**]()




- ከልጆችዎ ጋር የዳይኖሰር ምስሎችን ይመልከቱና ስለ ልዩ ልዩ የዳይኖሰር አይነቶችና ስለ ገጽታቸው ለምሳሌ ረጅም አንገት፣ ስለታማ ጥርስ ተውያዩ። በመቀጠል ልጆችዎ **የራሳቸውን ዳይኖሰር መሳል ትችላላችሁ። ነገ አብረን ዳይኖሰሩን እንሰራዋለን** ብለው ይንገሯቸው።
- ልጆችዎ የራሳቸውን ዳይኖሰር ዲዛይን እንዲያደርጉና እንዲስሉ ያድርጓቸው።
- በመቀጠል **የዳይኖሰራችሁ ስም ማነው? ምን ዓይነት ግጽታ አላቸው? ለመስራት ምን ምን ዕቃዎች ያስፈልጉናል** በማለት ይጠይቋቸው። ልጆችዎ በቤት ውስጥ ያሉ እቃዎችን (ለምሳሌ፥ አሮጌ ጨርቆች ወይም ጥጥ ለጸጉር፣ ለረጅሙ አንገት ጥቅል የእጅ ወረቀት ይቁረጡ) እንዲያስታውሱ ያግዟቸው። የተሰራው ስዕል ለቀጣዩ ቀን ይቀመጥ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ




## እውቀት፥ የድምጽ ቀለምን ተከትሎ መሬት መምታት

- እንዲህ ይበሉ፣ **እስኪ ቃላትን ወደ የድምጽ ቀለም ስንከፋፍል እንደ ትልቅ ዳይኖሰር መሬቱን በእግራችን እንምታ።**
- እንዲህ ይበሉ፣ በ **puppy መሬቱን በእግራችን እንምታ pup** (እንረፍ) **py**። **በ puppy ውስጥ ስንት የቃላት ቀለም አሉ? አዎ፣ 2! Pup - py , Pup – py**።
- **አሁን እናንተ ሞክሩ። በpurple የድምጽ ቀለም መሬቱን በእግራችን እንምታ (**pur **-** ple)። በparty (par **–** ty)
- ይህ ጨዋታ ለልጆችዎ ከቀለላቸው የራሳቸውን ሁለት የድምጽ ቀለም ያላቸው ቃላት እንዲያስቡ ይጠይቋቸው ወይም ባለ ሶስት የድምጽ ቀለም ቃላት (cu-cum-ber, fa-mi-ly) እርስዎ ይስጧቸው።

## ያንብቡ፥ ዳይኖሰር እወዳለሁ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *I Love Dinosaurs/ዳይኖሰር እወዳለሁ*

- ከልጆችዎ ጋር ዳይኖሰር እወዳለሁን ያንብቡ።
- በመቀጠል፣ **ከዳይኖሰር ጋር መኖሮ ምን አይነት ስሜት የሚፈጥር ይመስላችኋል**? ብለው ልጆችውን ይጠይቁ።




አፕልትሪ ኢንስቲትዩት ለትምህርት
ፈጠራ ምስል በ ክርስቲን አካምፒራ

(I Love Dinosaurs)
ዳይኖሰሮችን እወዳለሁ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 Unit 8 Week 2 Day 8

## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ቦታችንን እንያዝ!


- ለልጆችዎ **ወደተለያዩ ቦታዎች እንንቀሳቀስ ይበሏቸው**። ወደ ሌላ ቦታ ስለመጠጋት የመሳሰሉ ትዕዛዞች ለምሳሌ ወደ በሩ ጠጋ በሉ፣ እጃችሁን ከእራሳችሁ በላይ አድርጋችሁ ዝለሉ፣ ከጠረጴዛው ጎን ሆናችሁ ጨፍሩ። ብለው ትዕዛዝ ይስጧቸው።
- ልጆችዎ ትዕዛዝ እንዲሰጡ ሚና ተቀያየሩ።

## በጋራ መማር፥ የጓደኝነት ስዕል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር ወይም ጠፍጣፋ ቅርጽ ያለው ዉሃማ ቀለም ያለው ሰሌዳ**

- ጥሩ ጓደኞች የሚሰሯቸውን እንደ ማጋራት፣ ተራን መጠበቅ፣ ሲያዝኑ መልካም ነገሮችን መናገር የመሳሰሉ ነገሮችን ከልጆችዎ ጋር ይወያዩ። **ጓደኞሞች እርስ በርሳቸው ይተዋወቃሉ በጣም ይዋደዳሉ እንዲሁም ጊዚያቸውን አብረው በማሳለፍ ይደሰታሉ። እርስ በርሳቸው ይተዛዘናሉ ይረዳዳሉም። ጥሩ ጓደኞሞች የሆንበትን ጊዜ ወይም ለእኛ ጥሩ ጓደኛችን የነበርን ሰው እንሳል።ይህንን በግድግዳ ላይ ያለውን ምስል በቀጣይ አብረን እንሰራዋለን።**
- ግድግዳ ላይ ስዕሉን ከሳላችሁ በኋላ ሰለሳላችሁት ስዕልና ጓደኝነትን እንዴት እንደሚገልጽ አብራችሁ ተወያዩ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




(ዲፕሎዶከስ)
Diplodocus



Brachiosaurus (ብራቺኦስረስ)



Sinosauropteryx (ሲኖሳሮፕተሪ)



Stegosaurus (ስቴጎሳረስ)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




(ታይራኖሳረስ ሬክስ)
Tyrannosaurus Rex



Ornitholeste… (ኦርኒቶሌስትስ)



Triceratops (ቲሴ ራቶፕስ)



Ankylosaurus (አክሎሳረስ)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሃሙስ



## **STEM:** የራስን ዳይኖሰር መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ትናንት የተሳለው ዳይኖሰር፣ በህጻናት ምክረ ሃሳብ መሰረት ዳይኖሰር ለመስራት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ለምሳሌ የተጠቀለለ ወረቀት፣ ላስትሮ፣ ላባ፣ የመጫዎቻ ሊጥ ወይም [የመጨዋቻ ሊጥ አሰራር]።**

- ከልጆችዎ ጋር በፊት ስለሳሉት ዳይኖሰር ተነጋገሩ። **ልጆችዎን ዳይኖሰራችሁን አሁን እንስራ ይህን ለማድረግ ስዕላችሁን መጠቀም ትችላላችሁ ለዚህም እኔ አግዛችኋለሁ** ይበሏቸው።
- ዳይኖሰሩን በምትሰሩበት ጊዜ የመሪነት ሚናውን ልጆችዎ እንዲወጡ ይፍቀዱላቸው።


በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨውን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

©2020. AcceleTree Institute. All Rights Reserved.

በመጨዋቻ ሊጥ የምግብ ዝግጅት (FE)

## በግል መማር፡ የዳይኖሰር እንቁላሎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ጠፍጣፋ ቅርጽ ያለው ዉሃማ ቀለም ያለው ሰሌዳ፣ ላስትሮ፣ የመጫዎቻ ሊጥ ወይም [የመጨዋቻ ሊጥ አሰራር]**

- ልጆችዎን **ዳይኖሰሮች ልክ እንደ ወፎች፣ እንሽላሊቶች፣ አዞዎች እና ተሳቢ እንስሳት እንቁላል የሚጥሉ ተሳቢ እንስሳት ነበሩ** ይበሏቸው። **ዳይኖሰሮች ከረጂም ዓመት በፊት ይኖሩ የነበሩ አሁን ግን የጠፉ እንስሳት ናቸው። ከዚህ በኋላም አይኖሩም።**
- **ጥቂት የዳይኖሰር እንቁላል ቅሪት አካላት ብቻ ነው ያሉን። ዳይኖሰሮቹ ምን እንደሚመስሉም እርግጠኞች አይደለንም።የዳይኖሰር እንቁላሎችን ሰርታችሁ ምን እንደሚመስሉ መምርጥ ትችላላችሁ።**
- ልጆችዎ የመጫዎቻ ሊጥን ወይም የተጠቀለለ ወረቀትን፣ ላስትሮን እና ቀለምን በመጠቀም እንቁላሎቹን እንዲሰሩ ይፍቀዱላቸው።
- በመቀጠል ልጆችዎ **ስለሰሯቸው እንቁላሎችና ከእንቁላሎቹ ውስጥ ምን ዓይነት ዳይኖሰሮች ሊፈለፈሉ እንደሚችሉ** ይጠይቋቸው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 2 ቀን 9

## እውቀት፥ እስኪ ስለዳይኖሰሮች እንወያይ

- ለልጆችዎ **ስለ ዳይኖሰሮች ተምረናል። ዳይኖሰሮች በአሁኑ ጊዜ ይኖራሉ? ወይስ ጠፍተዋል?** ይበሏቸው።
- ልጆችዎን ከ 2 እስከ 3 ተከታይ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፣ **ዳይኖሰሮች እስካሁን ቢኖሩ ኖሮ ምን ታስቡ ነበር? ወይም የናንተ የዳይኖሶ ምርጫ ምን ዓይነት ነው?** እየተመላለሳችሁ ውይይቶችን ማድረግን ተለማመዱ።
- ልጆችዎ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ማውራት ካልፈለጉ በምትኩ ምን ዓይነት ጉዳዮች ላይ ማውራት እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸው።

## የጆርናል ሙከራ፥ የዳይኖሰር አጥንት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር፣ እርሳስ፣ ቅሪት አካላት, የቅሪት አካል መፈጠር, የቅሪት አካል የጆርናል ገጽ**

- ስዕልና ዲያግራም በጠቀም ስለቅሪት አካላትና የዳይኖሰር አጥንቶች ተወያዩ። ሰለ ዳይኖሰር አጥንቶች ያሚያሳዩ ሙዚየሞችን ወይም አጥንት ስለሚያጠኑ ተመራማሪዎችም መወያየት ትችላላችሁ።
- ልጆችዎ ስለዚህ ጉዳይ ስዕል እንዲስሉ እና ጽሁፍ እንዲጽፉ ያድርጓቸው።
- በመቀጠል **የዳይኖሰር አጥንት ብታገኙ ምን ታደርጉታላችሁ ብለው** ይጠይቋቸው።


ስም፡ ________________
የዳይኖሰር አጥንት ብታገኙ ምን ታደርጉታላችሁ?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

የዳይኖሰር አጥንት ብታገኙ ምን ታደርጉታላችሁ?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ




## STEM: ስንት ዕቃዎች አሉ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የቤት ዕቃዎች ለስላሳና ክብ የሆኑ ዕቃዎች ወይም ማንኪያዎች፣ እያንዳንዳቸው በቁጥር 10**

- ለልጆችዎ 9 ከለሮችን ያሳዩዋቸውና **ስንት ከለሮች አሉ?** ብለው ይጠይቋቸው። እርዳታን ከፈለጉ ወደእያንዳንዱ ከለር እየጠቆሙ አብረው በመቁጠር ያሳዩዋቸው።
- ይህንን ጨዋታ ከ0 እስከ 10 ላሉ ቁጥሮች ከ 2 እስክ 3 ጊዜ ደጋግመው ያጫውቷቸው። እንዲረዱት ለማገዝ የመጨረሻውን ድምር ይንገሯቸው ለምሳሌ **5 ከለርዎች አሏችሁ ይነሏቸው**።
- ልጆችዎ ከ 0 እስከ 10 ያሉ እቃዎችን ከቤትዎ ዙሪያ ሊያያመጡ ይችላሉ።

## በግል መማር: ለስላሳ ዳይኖሰርን መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Wooly Mammoth/ዉዲ ማሞዝ, ከለር ወይም ቀለም፣ ማጣበቂያ፣ የማስዋቢያ ነገሮች፡ ይጥጥ ኳሶች፣ ሳር፣ ክብ የዓይን ቅርጽ፣ ወዘተ



- ልጆችዎን እንዲህ ብለው ይንገሯቸው፣ **ባለ ለስላሳ ጽጉር ዳይኖሰሮች ከብዙ ብዙ ዓመታት በፊት ይኖሩ የነበሩ አሁን ግን የጠፉ ትላልቅ እንስሳት ነበሩ። እንደ ሱፍ ለስላሳ የሆነ ጸጉር ነበራቸው። የራሳችሁን ባለ ለስላሳ ጸጉር ዳይኖሰር መስራትና ማስዋብ ትችላላችሁ።**
- ለልጆችዎ የራሳችውን ባለ ለስላሳ ጸጉር ዳይኖሰር እንዲሰሩ ይፍቀዱላቸው።
- **እውነተኛ ባለ ለስላሳ ጸጉር ዳይኖሰር በትያዩ ምን ታስባላችሁ** በለው የጠይቋቸው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## እውቀት፥ ስለምወደው መጽሃፍ በቃል መናገር


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ህጻናት የሚወዱት የታሪክ መጽሃፍ ወይም በደንብ የሚያወቁት መጽሃፍ**

- ለልጆችዎ **ይህን መጽሃፍ ብዙ አንብበነዋል። በዚህ ታሪክ ውስጥ የተከሰቱ ሁለት ታሪኮችን ትነግሩኛላችሁ፡ መጀመሪያ ምን ተከሰተ? ቀጥሎስ?** በለው ይጠይቋቸው።
- ልጆችዎ እርዳታን ከፈለጉ ምስሎችን በመጠቀም ምን እንደተከሰተ ይከልሱላቸው። በመቀጠል ልጆችዎ የሚያስታውሷቸውን ሁለት ነገሮች ይጠይቋቸው።

## ያንብቡ፥ ዳይኖሰር እወዳለሁ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [I Love Dinosaurs/ዳይኖሰር እወዳለሁ]

- ከልጆችዎ ጋር ዳይኖሰር እወዳለሁ መጽሃፍን በጋራ ያንብቡ።
- በመቀጠል **ዳይኖሰር ብትሆኑ ኖሮ ምን ዓይነት ዳይኖሰር መሆን ትወዱ ነበር? ለምን?** ብለው ልጆችዎን ይጠይቁ።




አፕልትሪ ኢንስቲትዩት ለትምህርት
ፈጠራ ምስል በ ክርስቲን አካምፒራ
(I Love Dinosaurs)
**ዳይኖሰሮችን እወዳለሁ**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



**PK3 ስለ ዳይኖሰሮችና ቅሪት አካሎች በተመለከተ** **ውሊ ማሞዝ (FE)**

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 3



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 8 ሳምንት 3 ምልከታ

## እኔ ስነ-ቅሪት አጥኚ/ፓሊዮንቶሎጂስት ነኝ

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጆችዎ፡ እስከ አስር የሚደርሱ ቁሶችን ይቆጥራሉ፣ ከ3-5 ያሉ ቁጥሮችን ይለያሉ፣ሁለት ተከታታይ ደረጃ ያላቻዉን መመሪያዎችን ይፈጽማሉ እንዲሁም ስለዳይኖሰር የሚያጠኑ ስነ-ቅሪት ተመራማሪዎች ወይም ፓሊዮንቶሎጂስቶች ይማራሉ። ለልጆችዎ መመሪያዎችን በመስጠት፣ ግዴታዎን እንዲወጡ ትብብር በመጠየቅ ወይም ከ3-5 ያሉ ቁጥሮችን በአኩኩሉ መልክ ቤቱን እየተሸከረከሩ እንዲማሩ በማድረግ እነዚህን ተግባራት በተጨማሪነት ማከናወን ይችላሉ።



### ቁልፍ ቃላት



## ዳይኖሰር

በጣም ከብዙ አመታት በፊት ይኖር የነበረና አሁን ግን ከምድረ ገጽ የጠፋ ተሳቢ እንስሳ ነው



## ቅሪት አካል

በድንጋይ ውስጥ ተጠብቀው የተቀመጡ እንስሳት ወይም ዕጽዋት



## የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ

ስለ ቅሪት አካላት የሚያጠና ሰው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለዚህ ቅሪተ አካል የሚያጠኑ፣ የሚመራመሩ ወይም የሚማሩት ስለቅሪተ አካል ተመራማሪዎች ወይም ፓሊዮንቶጂስቶች ይማራሉ። ጥቅሉን ከመጀመርዎ በፊት፣ ሳይንቲስት ብትሆኑ ኖሮ ማወቅ ስለምትፈልጉት ነገር ጻፉ እና ስዕል ይሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## STEM: ቁጥሮችን መፈለግ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ3-5 ባሉ ቁጥሮች ከዚህ በፊት የተዘጋጁ ካርዶች፣ ያገለገለ ወረቀት ወይም ጋዜጣ፣ እቃ መያዣ፣ ሳጥን ወይም ቅርጫት፣** *በአማራጭነት አነስተኛ አካፋ ወይም ትልቅ ማንኪያ።*

- እንዲህ ይበሉ፣ **የቅሪተ አካል ተመራማሪ ወይም ፓንትዮሎጂስት ለመሆን ፈለጋችሁ፣ እናም ቁጥሮችን ፈልጉ።**
- **መጀመሪያ እስቲ ጥቂት ወረቀቶችን እንቅደድ።** ከዚያም እናንተ ጥር ያለባቸውን ሳጥኖች እንዲትፈልጉ እንደብቃቸዋል። **ልጅዎ ወረቀቶቹን በትናንሹ በመቀዳድ በእቃ መያዣ ውስጥ አስቀምጠዋል። ከዚያም በእቃ መያዣው ውስጥ ካርዶቹን ቁጥር እየሰጡዋቸው ይጨምሩ።**
- ልጅዎ ካርዶቹን እንዲፈልጉ በማድረግ ያገኙትን ቁጥር እንዲጠሩዋቸው ያድርጉ።

## በግል መማር: የኔ የዳይኖሰር የቤት እንስሳ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር/ክራዮንስ፣ወረቀት፣** ***እንደ አማራጭ-ሌሎች ማስጌጫ ቁሳቁሶች፣ ለምሳሌ- በክብ ቅርጽ የተሰሩ ቁሶች ወይም ዊግሊ አይስ፣ ያገለገሉ ወረቀቶች፣ የተቆራረጡ ጭርቆች።***

- የዳይኖሰር ግልገል ልጅዎ በማግኘቱ የተሰማውን ደስታ ወይም ስሜትን በተመለከተ ከልጅዎ ጋር ይወያዩ። **የዳይኖሰር ግለገል በማግኘቱ ምን ተሰማው? ምን አይነት ዳይኖሰር ሊሆን ይችላል? አብራችሁ ምን ማድረግ ትችላላችሁ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎ የዳይኖሰር ግለግል ምስል እንዲስል እድል በመስጠት ከዳኖሰር ግልገል ጋር ምን ማድረግ እንሚችሉ ያጽፏቸው።
- ከዚያም **ስለዳይኖሰር ግለገል ንገረኝ? አብራችሁ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ?** በማለት ይጠይቁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## እውቀት፥ ቩ ምን እየተሰማው ነው?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *The Little Beetle/ዘ ሊትል ቢትል*, ወረቀት፣ ከለር/ክራዮንስ**




- ከዘሊትል ቢትል ከገጽ 10-11 ያለውን ለልጅዎ ያሳዩ። **ቩን ተመልከት፣ ምን አይነት ስሜት እየተሰማው ይመስልሃል? እንዴት ለመንገር አስበሃል? አዎ የተበሳጨ ይመስላል፣ ፊቱ የንዴት ይመስላል፣ ስትናደድ ምን ትመስላለህ?**
- **ከዚህ በፊት ተበሳጭታሁ የነበረበት ጊዜን በተመለከተ መሳልና መጻፍ ትችላላችሁ።** በመሆኑም ልጅዎ ይህንን ተግባር እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት።
- **ከዚያም በተናደድህ ጊዜ ምን እንደሚሰማህ ንግረኝ?** በማለት ይጠይቁ። **በተናደደድህ ጊዜ ሰውነትህ ምን ይሰማው ነበር? እንደዚህ አይነት ስሜት ሲሰማህ ምን ታደርግ ነበር?**

## ያንብቡ፥ በብዙ መንገድ መቁጠር እችላለሁ የሚል መጽሃፍ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *I Can Count Lots of Ways/ በብዙ መንገድ መቁጠር እችላለሁ የሚል መጽሃፍ*!**




- ከልጅዎ ጋር በመሆን *I Can Count Lots of Ways! ያንብቡ።*
- ከዚያም፣ ገጽ 4-5 ያሳዩ፣ **በእነዚህ የድቦች ስብስብ ውስጥ ስንት ድቦች ይገኛሉ? በማለት ይጠይቁ። አዎ ሶስት ድቦች። አሁን ሶስት ድቦች ብቻ እስካሉ ድረስ በፍጥነት ልንቆጥራቸው እንችላለን።**

አስፓክለር መተግበሪያ ውስጥ በመግባት “Tips for Adult” ክፍል ውስ ስለቅሪት አካልና ዳይኖሰር በድምጽ የተቀረጸውን መጽሃፍ ማግኘት ይችላሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## STEM: እስቲ ቅሪተ አካሎችን እንስራ





**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ፈሳሽ ማጣበቂያ፣ለቅርጽ ማውጫ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች: ለምሳሌ:- እንጨት/ተዊግ፣ የእንስሳት ቅርፊት፣ ሹካ፣ የመጫወቻ ጭቃ ወይም [የመጫወቻ ጭቃ አሰራር]**

- እንዲህ ይበሉ፣ **የቅሪተ አካል ቅርጽ ልንሰራ ነው። ማጣበቂያው በሚሰራው ቅሪተ አካል ውስጥ ያለውን ክፍት ቦታ በመሙላት የሚያነክረውን አፈር አድርገን እንወስዳለን።** ልጅዎ በመጫወቻው ጭቃ ውስጥ አንድ ቁስ እንዲያስገቡ ያድርጓቸው። ግን ደግም ጭቃው ቶሎ እንዲደርቅ በጣም ወደ ወስጥ መግባት የለበትም።
- የጭቃው ቅርጽ እንዲወጣ ቁሱን ማውጣት። በተፈጠረው ቅርጽ ውስጥ ፈጸሳሹን ማጣበቂያ እንዲጨምሩ ልጅዎን ይፍቀዱለት። የመጫወቻ ጭቃውን እና ማጣበቂያው ለመድረቅ በቂ ጊዜ እንዲያገኝ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ መጠበቅ ሊያስፈልግዎ ይችላል።
- ማጣበቂየያው ከደረቀ በኋላ የተፈጠረውን ቅርጽ ለማግኘት በጥንቃቄ ማጣበቂያውን ይላጡ።
- ከዚያም የተፈጠረውን ቅርጽ ከዋናው ቁስ ቅርጽ እና ከጭቃ መጫወቻ ውስጥ ያለውን ሞልድ ወይም ቅርጽ ማውጫ ጋር አመሳክሩት።

## በግል መማር: የዳይኖሰር እግር ዱካ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [ቅሪት አካላት], በዳኖሰር እግር ዱካ ቅርጽ የተቆራረጡ አሮጌ አስፖንጅ፣ የውሃ ቀለም ማቀነባበሪያ ዝርግ እንጨት፣ ወይንም የመጫወቻ ጭቃ ወይም [የመጫወቻ ጭቃ አሰራር]**



- እንዲህ ይበሉ፣ **ዳይኖሰሮች ከምድረ ገጽ የጠፉ ወይም በህይወት ያሉ ባይሆንም የስነ ቅሪት ተመራማሪዎች የእግር ዱካቸውን በመመልከት ብዙ ነገሮችን መማር ይችላሉ።** የዳይኖሰር ዱካና እግርን ያሳዩ።
- **እስቲ የዳይኖሰር የእግር ዱካን እንስራ!** እስፖንጁን ወይንም ጣቶችን (ሶስት የመሃል ጣቶች ወይም ሁለት የጣት ጫፎች) እንዴት አድርጎ መጫን እንዳለበት ማስተካከል እና የእግር ዱካውን ለመስራት በቀለሙ ውስጥ በመንከር እና ወረቀት ወይም የመጫወቻ ጭቃው ላይ መጫን።

- የተለያዩ ዱካዎችን በመጠቀም ልጅዎ ሙከራ እንዲያደርግ ይፍቀዱ። ከዚያም **ምን አይነት የእግር ዱካ ነው የሰራሃው?** በማለት ይጠይቁ። **የዳይኖሰር የእግር ዱካ ምን ያህል ሊተልቅ ይችላል ብለህ ታስባለህ?**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ ስለቀን ውሎህ ንገረኝ

- ስለቀን ውሎው ከልጅዎ ጋር ይወያዩ። በበቀን ውሎው ውስጥ የገጠመውን ሁለት ነገሮችን በቅደም ተከተል እንዲነግሯችሁ ይጠይቁ።
- **በዛሬው ቀን ምን እየሰራህ እንደዋልክ ልትነግረኝ ትችላለህ? ከዚያም በኋላ ምን ስትሰራ ነበር?** በማለት ይጠይቁ።
- *እንደ አማራጭ- ልጅዎ ካከናወኗቸው ነገሮች ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን መሳል ይችላል።*

## የጆርናል ሙከራ፥ የዳይኖሰር እንቁላል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ባለቀለም እርሳሲች፣ እርሳስ፣ የዳይኖሰር እንቁላል ጆርናል ገጽ**

- ዳይኖሰሮች ከእንቁላል በመፈልፈል ስለመፈጠራቸው ከልጅዎ ጋር ይወያዩ።
- ልጅዎ ስለ፲ጉዳዩ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- ከቀይታ በኋላም፣ **የዳይኖሰር እንቁላል ብታገኝ ምን ታደርጋለህ?** ብለው ይጠይቁ።


ስም፥ ___________________

የተፈሰፈለ የዳይኖሰር እንቁላል ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

የተፈለፈለ የዳይኖሰር እንቁላል ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ




## STEM: ስንት ጣቶች ናቸው?

- ስምንት ጣቶችን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ **ስንት ጣቶች ናቸው ያሉኝ?** በማለት ይጠይቁ። ልጅዎ ጣትዎን እንዲቆጥር ያድርጉ። ከዚያም ተመሳሳይ ቁጥር ያለውን ጣት እጃቸውን ከፍ በማድረግ እንዲያሳዩ ያድርጉ። በአጠቃላይ ስንት ጣቶች እንዳሏቸው ልጅዎን ይጠይቁ። መመለስ ካልቻሉ ወይም እንደገና መቆጠር ካለበት፣ ከእንደገና ሁሉንም በመድገም **ስምንት ጣቶች ናቸው** በማለት ይንገሩ። ይህም በመጨረሻ የተቆጠረው ቁጥር ከጠቅላላው ጋር ተመሳሳይ ስለመሆኑ እንዲረዱ ለማገዝ ነው።
- ከ0 (ቡጢዎን ያሳዩ) እስከ 10 ያሉትን ቁጥሮች የእርስዎን ጭብጥ እጅ በማሳየት ከ3-4 ጊዜ እንደአስፈላጊነቱም ሁሉንም ቁጥር በመደጋገም ያሳዩ።



## በግል መማር: የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ እንቆቅልሽ

***አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ እንቆቅልሽ](), በህጻናት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መቀሶች፣ እንደ አማራጭ- ቁርጥራጮቹን ከማቅለማችሁና ቆራርጣችሁ ከማውጣታችሁ በፊት ልክ እን ጥራጥሬ ማሸጊያ በካርድቦርዱ ላይ የስነ ቅርስ ተመራማሪዎች እንቆቅልሹን በማጣበቂያ ያጣብቁ፣***



- **የስነ ቅርስ ተመራማሪ ማለት ስለዳይኖሰሮች የሚያጠና ሳይንቲስት ማለት ነው** ብለው ይንገሩ።
- ቁርጥራጮቹን ቆራርጠው ለማውጣት ከመርዳትዎ በፊት ልጅዎ እንቆቅልሹን እንዲያቀልም ያድርጉ።ከዚያም እንቆቅልሾቹን አንድላይ ያስቀምጡ።
- ከዚያም **የስነ ቅሪት ተመራማሪ/የዳይኖሰር ተመራማሪ መሆን ምን አይነት ስሜት ይኖራል ብላችሁ ታስባላችሁ? በማለት ጠይቋቸው።**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 3 ቀን 13

## እውቀት፥ መልካም ቃላት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ የቀለም እርሳሶች ወይም የወሃ ቀለም መቀለሚያ**

- **አንዳነድ ጊዜ ችግር ሲያጋጥመን ልንበሳጭ እንችላለን። አንድ ሰው ላይለመቀለድ ወይም ለማሾፍ ፈልገን ይሆናል። መልካም ያልሆኑ ቃላትን ላንጠቀም እንችላለን፡ በማለት ይናገሩ።** ስለመልካም ያልሆኑ ቃላት እና እንድ ሰው እነዚህን መልካም ያልሆኑ ቃላትን ለልጅዎ ቢናገር ሊሰማው በሚችለው ጉዳይ ላይ ከልጅዎ ጋር ይወያዩ።
- **መልካም ያልሆኑ ቃላትን ከመጠቀም ይልቅ በጎና መልካም ቃላትን መጠቀም አለብን። መልካም ቃላትን በምትጠቀም ጊዜ ብስጭት የሚሰማህከሆነ ንዴትህ እስኪበርድልህ ድረስ ምንም አይነት ቃላትን አትናገር።**
- ልጅዎ ስለሚጠቀሙት መልካም ቃላት እንዲስሉና እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ከዚያም **መጠቀም ስለምትችለው መልካም ቃላት ንገረኝ** በማለት ይጠይቁ።

## ያንብቡ፥ በብዙ መንገድ መቁጠር እችላሁ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*I Can Count Lots of Ways/ በብዙ መንገድ መቁጠር እችላሁ*]!




- ከልጅዎ ጋር በመሆን *በብዙ መንገድ መቁጠር እችላለሁ/I Can Count Lots of Ways! ያንብቡ።*
- በኋላም ከገጽ 6-7 ያለውን ያሳዩ። **አያያዥ ሰንሰለቶቹን አንድ በአንድ መቁጠር ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁ። ከዚያም በሁለት ሁለት ወይም ጥንድ እንዴት መቁጠር እንደሚቻል በማሳየት **አንድ በአንድ ከመቁጠር እጅጉን የፈጠነ ነው!** ይበሉ።
- ይህ በሁለት ሁለት ወይም ጥንድ ለመቁጠር መግቢያ ነው። ልጅዎ በሁለት ሁለት ወይም ጥንድ ለመቁጠር ገና ስለሆነ አሰፈላጊም አይደለም።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 3 ቀን 13

## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ የስነ ቅሪት/ዳይኖሰር ተመራማሪው ፒት


- እንዲህ ይበሉ፣ **ልክ እንደ ሳይመን እንዲህ አለ አይነት አይነት ጨዋታ እስቲ እንጫወት። ግን በአሁን ሰዓት የስን ቅሪት/ዳይኖሰር አጥኚው ፒት መፈጸም ያለባችሁን መመሪያ ይሰጣችኋል። “ፒት እንዲህ አለ” የሚለውን ስትሰማ ብቻ ትዕዛዛቱን ፈጽማቸው።**
- **ፒት እንዲህ አለ ወደላይ ከዘለላችሁ በኋላ አጓሩ፣ ወይም የዳይኖሰር አጥንቶችን የምትፍሩ በማስመሰል አጽዷቸው፣ ወዘተ...** የመሳሰሉ ባለ ሁለት ተከታታይ ደረጃ ያለው መመሪያ ስጧቸው።
- ልጅዎ ትዕዛዝ መስጠት እንዲችል ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## በጋራ መማር፥ ምን ማግኘት ነው የምትፈልገው

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለር**

- ልክ የሰነ ቅሪት/ዳይኖሰር ተመራማሪው የዳይኖሰር አጥንት ወይም ሌሎች ቅሪተ አካላትን ለማግኘት እንደሚፈልገው አይነት (የግድ ከዳይኖሰር ጋር ብቻ መገናኘት የለበትም) ከልጅዎ ጋር ሁለታችሁም ማግኘት ስለምትፈልጉት ነገር ይወያዩ።
- የት መፈለግ እንዳለባችሁ ተወያዩ። ከዚያም ሁለታችሁም የምትፈልጉትን ነገር ለማግኘት ስለቁሱ ስዕል ለመሳል በጋራ አንድ ላይ ስሩ። ስታገኙት ምን ሊሳማችሁ እንደሚችል ጉዳይ ላይ ተወያዩ።
- ስለምትፈልጉት ነገር ጉዳይ ከኢንተርኔት በመፈለግ ወይም መጸረሃፍ በማንበብ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 3 ቀን 14

## **STEM:** አፈር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በእኩል ግማሽ የታጠፈ ወረቀት፣ ከለር፣ አፈር፣ ብርሃን አስተላላፊ የውሃ መያዣ ወይም ጄሪካን ከክዳን ጋር(ወይም ክዳን ከሌለ ውሃውን ከመበጥበጥ ይልቅ ማማሰል)፣ ውሃ፣ *እንደ አማራጭ - አፈር ማግኘት ካልተቻለ እንደ ብኪንገ ሶዳ(እርሾ) ጨው፣ ወይም የውሃ ይዘት ማሻሻያ ያሉ ንጥረ ነገሮችን በመጨመር የሚችሉ ሲሆን ከዚያም ስለብክለቱ ይወያዩ።***

- እንዲህ ይበሉ፣ **አፈር ወይም ቆሻሻ ከብዙ ነገሮች ነው የሚሰራው። በማበስበሻው ቦታ ላይ ሹ የሚበላው መጨረሻ ላይ አፈር ይሆናል። በአፈር ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ነገሮችን ለማየት እስቲ ሙከራ እንስራ።**
- ጄሪካኑን እስከ ግማሹ ድረስ አፈር እንዲሞሉ ልጅዎትን ይፍቀዱላቸው። አንድ ኢንች የአየር ክፍተት እስኪኖረው ድረስ ውሃ ሙሉበት። ጄሪካኑን በመክደን ልጅዎ አፈሩ በደንብ እስኪሟሟ ድረስ እንበጠብጡ ይዘዙ። **አፈርና ውሃውን ለትንሽ ጊዜ ቢተው ምን ሊፈጠር ይችላል?** በማለት ይጠይቁ።
- በአንዱ ግማሽ ወረቀት ላይ ልጆችዎ ምን እንደተገነዘቡ በስዕል እንዲገለጹ ያስሏቸው።.
- ጄሪካኑን ለጥቂት ሰዓታት ወይም ሌሊቱን በሙሉ ሳይነካ ያቆዩት። ከዚያም የተለያዩ የአፈር ንብርብርን ለማየት አብራችሁ ተመልከቱ። ክብደት ያላቸው እንደ ኮረት ያሉ ቁሶች ወደ ታች ይሰምጣሉ። የሚቀጥለው ንብርብር ቀላል ክብደት ያላቸው እንደ አሸዋ እና ሸክላ እንዲሁም ሌሎች ነገሮች ካሉ ወደላይ ይንሳፈፋሉ። ልጅዎ በአንድ ግማሽ ወረቀት ላይ የንብርብሮቹን ስዕል እንዲስል እንዲስል ይፍቀዱላቸው።

## በግል መማር፡ የዳይኖሰር የእጅ አሻራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የውሃ ቀለም ማቅለሚያ ሳህን፣ ወረቀት፣ *እንደ አማራጭ- በቁመት የተቆራረጡ ወረቀቶች፣ በአይን ቅርጽ የተዘጋጁ ቅርጾች፣ ኩክ ማውጫ ያሉ ማስጌጫዎች፣ ወዘተ…***

- **የእጅ አሻራን በመጠቀም ዳይኖሰር መስራት ትችላለህ ብለው** ይንገሩት። እጆቻቸውን ለቅርጽ ማውጫነት እንዲዘጋጁ በማድረግ፣ ከዚያም ዳይኖሰሩን ለመስራት መዳፍን ወደታች በማዞር መጫን።
- ልጅዎ የእጅ አሻራ እንዲሰራ ያድርጉ፣ ከዚያም እንደ አይን፣ ቀንድ፣ ዝርግ ሳህን፣ እንዲሁም እነሱ የፈለጉትን ገጽታዎችን ይጨምሩበት።
- ከዚህ በኋላም **ስለዳይኖሰርህ ንገረኝ፣ ማን ተብሎ ይጠራል?** በማለት ይጠይቁ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## እውቀት፥ አስቂኝ መመሪያዎች

- **በጣም ቀላል የሆኑ መመሪዎችን ልሰጥህ ስለሆነ በደንብ እንትፈጽማቸው እፈልጋሉ፣ በጥሞና ተከታተል።** በማለት ይንገሩ።
- ለልጅዎ ሁለት ተከታታይ ደረጃ ያለው ቀላል መመሪያዎችን ይስጧዋቸው። ለምሳሌ- እንደ ዳይኖሰር አጓራ እና ጭራህን አወዛውዝ፣ ፈገግ በማለት የዳይኖሰር ድምጽ በማስመሰል ሰላም እንዲል ማድረግ።
- ልጅዎ መመሪያዎችን ለእርስዎ መስጠት እንዲችል ሃላፊነትን ይስጡ።

## የጆርናል ሙከራ፥ የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር፣ እርሳስ፣ የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ ጆርናል ገጽ**

- ስለጥንታዊ ቅሪተ አካሎች የሚያጠናውና የሚማረው የስነ ቅሪት/ዳይኖሰር አጥኚ መሆን ምን አይነት ስሜት ሊሰጥ በሚችል ጉዳይ ላይ ይወያዩ።
- ልጅዎ ስለጉዳዩ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- ከጥቂት ጊዜ በኋላም **የጥንታዊ የስነ ቅርስ ተመራማሪ/ፓሊዮንቶሎጂስት/ መሆንና ስለጥንታዊ ቅርስ መማር ምን አይነት ስሜት ይሰጣል?** በማለት ይጠይቁ።


ስም፡ ____________________

ስለቅሪት አካላት የሚያጠና ሳይንቲስት መሆን ምን አይነት ይመስላችኋል?

**PK3 ስለ ዳይኖሰሮችና ቅሪት አካሎች በተመለከተ**

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________


ስለቅሪት አካላት የሚያጠና ሳይንቲስት መሆን ምን አይነት ይመስላችኋል?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## **STEM:** የዳይኖሰር/ዳይኖ እንቁላል ስብስቦች




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** Dino Egg Sets/የዳይኖ እንቁላል ስብስቦች, **በላቀለም እርሳሶች፣ በህጻናት ላይ ጉዳት የማደርሱ መቀሶች**

- **በዚህ ገጽ ላይ ስንት የዳይኖሰር እንቁላል ስብስቦች እንዳሉ ለማወቅ ቁጠር** በማለት ይንገሩት።
- **አሁን እንቁላሎቹን በማቅለም በቅርጻቸው ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ።** አስፈላጊ ከሆነም ልጅዎ እንቁላሉን በቅርጹ ቆርጦ እንዲያወጣ ማገዝ ይችላሉ።
- ከዚያም የተለያዩ ቁጥር ያላቸውን እንቁላሎች ለይተው ያስቀምጡ፣ ለምሳሌ- 8 እንቁላሎች ወይም 5 እንቁላሎች፣ከዚያም ልጅዎ እንዲቆጥራቸው ይጠይቁ። ከቆጠረ በኋላም በአጠቃላይ ስንት እንቁላሎች እንዳሉ ልጅዎን ይጠይቁ። በትክክል መመለስ ካልቻሉ ወይም መቁጠር መጀመር ካቃታቸው በሰተመጨረሻ የተቆጠረው ሁሉም መሆኑን መገንዘብ እንዲችሉ ከዚህ በፊት የነበረውን አካሄድ ሁሉ ይድገሙት። ለምሳሌ **አዎ-አምስት እንቁላሎች አሉህ።**

## በግል መማር፡ ዳይኖሰሩን ማቅለም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** Dinosaur Coloring/ዳይኖሰርን ማቅለም, **የውሃ ቀለም መቀመሚያ ዝርግ ሳህን ወይም ባለቀለም እርሳሶች፣ *እንደ አማራጭ- ሌሎች ማስዋቢያዎች እንደ በቁመት የተቆራረጡ ወረቀቶች በአይን ቅርጽ የተሰሩ ቅርጾች፣ ጥጥ፣ ወዘተ ቁሶች***


ታይራኖሶረሱስ ሬክስ

- ልጅዎ ከስዕሉ ምን እንደተገነዘበ ይጠይቁት። ስጋ የሚበሉ ዳይኖሰሮች (ስጋ በሊታዎች) ሹል ጥርሶች አሏቸው። ተክል የሚመገቡ ዳይኖሰሮች (ተክል ተመጋቢዎች) ቅጠሎችን ደርሰው መቀንጠስ እንዲችሉ ረጃጅም አንገት አሏቸው።
- **ዳይኖሰሮች ምን አይነት የቆዳ ቀለም እንዳላቸው ወይም ቆዳቸው ምን አይነት እንደሆነ ለማወቅ እርግጠኛ አይደለንም። እንዚህን ዳይኖሰሮች በፈለጋችሁት መንገድ ማቅለምና ማጌጥ ጥችላለህ፣** በማለት ይንገሩት።
- ከዚያም በኋላ **ስለዳይኖሰርህ ንገረኝ!** በማለት ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## እውቀት፥ ጥሎ/ትቶ መሄድ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳሶች ወይም የውሃ ቀለም መቀመሚያ ዝርግ ሳህን፣**

- **ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደምንችል እየተወያየን ነበር። አንዳንዴ ትተን እንሄዳለን፣ በመሆኑም ችግሩ እየገዘፈ አይመጣም። አንድ ሰው በእኛ ላይ እያሾፈ ወይም መልካም ሊሆንልን ካልቻለ ትተነው መሄድ አለብን። አንድ ነገር ደህንነቱ ካልተረጋገጠ ትተነው በመሄድ እርዳታ ማግኘት አለብን።** ብለው ይንገሩት።
- **ችግር እንዳይፈጠር ወይም ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ትተህ የሄድክበትን ጊዜ ማስታወስ ትችላለህ?** በምሳሌ በመደገፍ ልምድህን ንገረኝ።
- ከዚያም በኋላ፣ ልጆችዎ የገጠሟቸውን ችግሮች ለመፍታት ወይም ችግር እንዳይፈጠር ትተው የሄዱበትን አጋጣሚ ወይም ችግር ሲፈጠር መቼ ትተው መሄድ እንዳለባቸው እንዲጽፉና እንዲስሉ ይፍቀዱላቸው።
- ከዚያም በኋላ **ትተህ የሄድክበትን ጊዜ ንገረኝ** በማለት ይጠይቁት።

## ያንብቡ፥ *በብዙ መንገድ ማንበብ እችላለሁ!*


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *I Can Count Lots of Ways/በብዙ መንገድ ማንበብ እችላለሁ!*

- ከልጅዎ ጋር *በብዙ መንገድ መቁጠር እችላለሁ!* የሚለውን መጽሃፍ *ያንብቡ።*
- ከዚያም በኋላ ገጽ 12-13 ያለውን ገጽ ያሳዩ። **የሚደንቅ ነው! ይህ ብዙ ኮከቦች ናቸው። እስከ 100 መቶ ድረስ አንድ በአንድ ለመቁጠር ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል፣ ግን ደግሞ በአስሮች በፍጥነት እንዴት መቀጠር እንደምችል እንይ እስቲ.** እያንዳንዱን አግድም በመጠቀም 10፣ 20፣ 30፣ ወዘተ… ይቁጠሩ። **ይሄ ከበፊቱ በጣም የፈጠነ ነው!** በማለት ይንገሩ።
- ይህ በአስሮች ለመቁጠር መግቢያ ነው። ልጅዎ አሁንም የግድ በአስሮች ለመቁጠር አስፈላጊ አይደለም።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



# ታይራኖሶረሱስ ሬክስ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ስቴጎሳውረስ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሳምንት 4


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ምልከታ

## የዳይኖሰር ቲያትር

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥



እስከ 10 የሚደርሱ ቁሶችን ይቆጥራል፣ ከ3-5 ያሉ ቁጥሮችን ለይቶ ያውቃል፣ እና ስለ ዳይኖሰር ይማራል። በተጨማሪም ምን እንደሚሰማቸው፣ እና ስለጓደኝነት እንዲሁም ተረት ተረት ደጋግመው ይናገራሉ። በቀን ውሏቸው ውስጥ ያጋጠሟቸውን ሁለት ክስተቶችን ልጆችዎን በመጠየቅ እና ደጋግመው በመንገር ልምምድ ማድረግ ይችላሉ።

### ቁልፍ ቃላት



## ዳይኖሰር

በጣም ከብዙ አመታት በፊት ይኖር የነበረና አሁን ግን ከምድረ ገጽ የጠፋ ተሳቢ እንስሳ ነው




## ስሜቶች

እንደ መደሰት እና ማዘን ያሉ ስሜቶች ናቸው



## ቅሪት አካል

በድንጋይ ውስጥ ተጠብቀው የተቀመጡ እንስሳት ወይም ዕጽዋት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

ስለዳይኖሰር ሁሉንም ነገር በመማር ይህ የመጨረሻው ሳምንታችሁ ነው! ጥቅል ትምህርታችሁን ከመጀመራችሁ በፊት በዚህ ሳምንት ስለአንድ ነገር መማር የምትፈልጉትን ጻፉ እንዲሁም ሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## STEM: ከ3-5 ማስታወስ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከቀን 5 ጀምሮ ከ3-5 ያለባቸው የካርድ ቁጥሮች**

- ልጅዎን የማዛመድ ጨዋታ እንዴት መጫወት እንደሚቻል ያሳዩ። ካርዶቹን ወደታች ገልብጠው ያስቀምጡ። ሁለትካርዶችን ገልብጠው ያስቀምጡ። ቁጥሮቹ የሚዛመዱ ከሆነ ቁጥሮቹን በመጥራት ከመጫወቻ ቦታቸው ውስጥ ካርዶቹን ያውጡ ወይም ያንሱት። ካርዶቹ የማይዛመዱ ከሆነ ደግሞ ካርዶቹን ወደታች እንደገና ገልብጠው ያስቀምጡ።
- ከልጅዎ ጋር ተጨማሪ የጨዋታ ዙር በማድረግ ሁሉም ቁጥሮች እስኪዛመዱ ድረስ ጨዋታውን ይጥሉ።
- ጨዋታው የበለጠ ፈታኝ እንዲሆን ተጨማሪ ቁጥሮችን ይቀላቅሉ!

## በግል መማር፡ አይሆንም ማለትን መቀበል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳሶች፣ ስሜቶች**

- **አንዳንድ ጊዜ አብሮ አደጎች ወይም ጓደኛሞች አይሆንምሊሉን ይችላሉ ምክንያቱ ደግሞ የሆነ ነገር አንዳንሰራ ወይም እንድንሰራ ነው። ጓደኛችን ከእኛ ጋር መጫወት ስለማይፈልግ እምቢ/አልፈልግም ሊሉን ይችላሉ፣ በማለት ይንገሯቸው።** ሰዎች እምቢ ወይም አይሆንም ሊሉ የሚችሉበት ጉዳይ ላይ አብራችሁ ተወያዩ፣ ለምሳሌ የሆነ ሰው ጥሩ ያልሆነ ወይም ጉዳጥ የሚያደርስ ነገርን እንድሰራ በሚፈልግበት ጊዜ፣ ወይም ለጤና ጥሩ ያልሆነ ነገርን ብሉ ስንባል።
- **አንድ ሰው አምቢ/አይሆንም ሲል ምን ይሰማሃል?** የመናደድ፣የመፍራት ወይ ሃዘን ሲሰማቸው ምን ሊሰማቸው እንደሚችልና ምን ሊያደርጉ በሚችሉ ነገሮች ላይአብራችሁ ተወያዩ። ምን ሊሰማቸው እንደሚችል መለየት እንዲችሉ በስሜት ስዕል በመጠቀም ይርዷቸው።
- አንድ ሰው እምቢ ወይም አይሆንም ሲሏቸው ይህንን ለመቀበል ምን ማድግ እንደሚችሉ በስዕልና በጽሁፍ እንዲገልጹ ልጆችዎን ይፍቀዱላቸው።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሰኞ



## እውቀት፥ የኔን መመሪያዎች/ትዕዛዞች ይከተሉ

- **መፈጸም ያለብህን መመሪያዎች ወይም ትዕዛዞችን አሁን እሰትሃለሁ፣ በጥሞና አዳምጥ ብለው ይንገሩ።**
- ሁለት ተከታታይ ደረጃ ያለውን ትዕዛዞች ለልጅዎ ይስጡ። ለምሳሌ- ማጓራትና ጥፍርህን ማሳየት፣ የዳይኖሰርህን ክንፍ ማራገብና መዝለል፣ አይንህን ጨፍኖ መክፈትና ፈገግ ማለት።
- ልጅዎ ትዕዛዝ መስጠት እንዲችል ሃላፊነት ይስጡዋቸው።
- ይህ ደግሞ ቀላል ከሆነ ስስት ተከታታይ ደረጃ ያለው ትዕዛዞችን ይስጧቸው።

## ያንብቡ፥ ***A Reef Tale/***ኤ ሪፍ ቴል




ኤ ሪፍ ቴል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***A Reef Tale/ኤ ሪፍ ቴል***

- ከልጅዎ ጋር ሆነው የባህር ውስጥ ተረት/*A Reef Tale ያንብቡ።*
- ከዚያም በኋላ፣ **አልፊ አይነስውር ነው ማለት ይቻላል፣ ይህ ማለት ደግሞ በደንብ ማየት ወይም መመልከት አይችልም ነው። በደንብ ማየት ባለመቻሉ ፈሪ እንዲሆን አድርጎታል። ኩዊንም ፈርታለች። እሷም ፈሪ የምትሆነው ለብቻዋን ስትሆን ነው።** ብለው ይንገሯቸው።
- **ፈርተህ የነበርክበትን ጊዜ ንገረኝ። ምን አይነት ስሜት እንዲሰማህ አድርጎሃል?** ልጅዎ ሰውነታቸው ምን እንደተሰማቸው እና ፊታቸው ላይ ምን አይነት ስሜት እንደተሰማው እንዲነገሯችሁ ያበረታቱ። የሚያስፈራ ፊት በማሳየት ፍራቻ ሲሰማዎት ምን አይነት ስሜት እንደተሰማዎ ይንገሯቸው።

በተጨማሪም፣ ለሁሉም መጻህፍት ቀድመው የተቀዱ ንባቦች ለአዋቂዎች ጠቃሚ ምክሮች /Tips for Adults፣ ዳይኖሰሮች እና ቅሪት አካላት በሚለው ስር በሚገኘው Sparkler መተግበሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ቀን 17

## STEM: እሳተ ጎመራ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ Volcanoes/እሳተ ጎመራ, ማንኪያ፣ ብርሃን አስተላላፊ ኩባያ ወይም ውሃ መያዣ፣ ከ4-5 ማንኪያ እርሾ/baking soda, 1 ማንኪያ ፈሳሽ የእቃ ማጠቢያ፣ 1 ኩባያ ኮምጣጤ፣ ለሙከራ መስሪያው ዝርግ ሳህን ወይም ሙከራውን ከገላ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ወይም ውጪ መስራት፣ *እንደ አማራጭ-የምግብ ማቅለሚያ***



- የእሳተ ጎመራ ስዕሎችን ይመልከቱ፣ **እሳተ ጎመራ ማለት በትልቅ ተራራ ጫፍ ላይ ያለ ሰፊ ጉድጓድ ሲሆን የቀለጠ አለትም በጉድጓዱ በኩል የሚወታበት ነው። ላቫ ማለት ደግሞ በጣም የሚያቃጥል የቀለጠ አለት ወይም ድንጋይ ነው። አንዳንድ ሰዎች ዳይኖሰሮች በሙሉ የሞቱት ወይም ከምድር ገጽ የጠፉት ግዙፍ እሳተ ጎመራ በመፈንዳቱ ምክንየት ነው ብለው ያስባሉ። ይህ ማለት ደግሞ በጣም ብዙ የሚያቃጥል የቀለጠ አለት ወይም ድንጋይ በመፈንዳት ዳይኖሰሮቹን ገደለ እንደማለት ነው። እስቲ ሙከራ በስራት አነስተኛ የገሞራ ፍንዳታ እንፍጠር።**
- በኩባያው ውስጥ ⅔ኛ ውሃ እንዲሞላ፣ የዳቦ እርሾ፣ የእቃ ማጠቢያ ሳሙና፣የምግብ ማቅለሚያ እንዲጨምርና እንዲያማስል ልጅዎን ያግዙ። ከዚያም የዳቦ እርሾውና ኮምጣጤው በሚቀላቀሉት/በሚዋሃዱበት ወቅት በሚፈጠር ጋዝ የሚከሰተውን ፍብዳታ ለማየት ኮምጣጠውን ይጨምሩበት። ይህ ጋዝም ነገሮች አረፋ እንደፈጠር የሚያደርግ ነው።
- ከዚያም በኋላ ልጅዎ ምን እንደተገነዘበ ለማወቅ አብረው ይወያ።
- ንጥረ ነገሮቹን ማግኘት ካልቻሉ፣ ከኢንተርኔት ላይ ሙከራውን ቪዲዮ ወይም የእሳተ ጎመራ ፍንዳታ ቪዲዮን መመልከት ይችላሉ።

## በግል መማር፡ ዳይኖሰር መገጣጠም 1-5

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ Dinosaur Puzzle/ዳይኖሰር መገጣጠም፣ ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - ቁርጥራጭ ወረቀት ካርቶን (ምሳ፡ የጥራጥሬ ሳጥን) ላይ ማጣበቂያ እና ቁርራጮቹን ቆርጦ ማውጫ***




- ለልጅዎ **ይህን የዳይኖሰር ቁርጥራጭ ቀለም መቀባትና አንድ ላይ መገጣጠም ትችላለህ። ይህኛው መገጣጠም ትንሽ ለየት ያለ ነው። ቁርጥራጮቹን ከ1 እስከ 5 በቅደም ተከተል አንድ ላይ ትገጣጥማለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን ቁርጥራጮቹን ቆርጦ በማውጣት ላይ ከመርዳትዎ በፊት ቀለም ቀለም እንዲቀባቸው ይፍቀዱለት። ከዚያም አንድ ላይ ይገጣጥማቸዋል።
- ከዚያም አንድ ላይ ቁጥሮችን ጠቁማችሁ እያሳያችሁ ከ1 እስከ 5 ቁጠሩ። ከዚያም ልጅዎን የተወሰነ ቁጥር ጠቁሞ እንዲያሳይ ይጠይቁት፣ **4 ቁጥርን ጠቁመህ አሳይ።**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ቀን 17

## እውቀት፥ ስሜቶቻችንን አስመስለን መተወን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** **ስሜቶች**



- ለልጅዎ **እስኪ የተለያዩ ስሜቶቻችንን አስመስለን እንተውን እና ምን እንደሆኑ እንገምት** ብለው ይንገሩት።
- ስሜትን የመተወን እና የመገመት ተራ ተቀያየሩ፣ ምሳ፡ ማዘን፣ መበሳጨት፣ መደሰት፣ መገረም ወይም መደነቅ
- በተጨማሪም ስሜት መምረጥ እና ያንን ስሜት ስለሚፈጥሩ ነገሮች መነጋገር ትችላችሁ፣ ምሳ፡ የልጅዎ አዲስ ነገር ሲያደርግ መደሰት ወይም የሆነ ሰው ሲያጣ ማዘን።


## የጆርናል ሙከራ፥ አይሆንም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የአይሆንም የጆርናል ገጽ**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የሆነን ሰው አይሆንም ስለሚልባቸው ጊዜያት ተነጋገሩ። እንግዳ ሰው የሆነ ነገር እንድናደርግ ሲጠይቀን ወይም ጓደኞችን ትክክል ያልሆነ ነገር (ምሳ፡ በሌላ ሰው ላይ ማሾፍ) እንድናደርግ ሲነግረን አይሆንም ማለት እንችላለን።
- ልጅዎ ስለዚህ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ አይሆንም ማለት ስለነበረብህ ጊዜ ንገረኝ። አይሆንም ብለህ ስትመልስ ምን አይነት ስሜት ተሰማህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________


ለሆነ ሰው አይሆንም የሚል ነገር ስለተናገራችሁበት ጊዜ ጻፉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## STEM: አሳ መቁጠር



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ Fish Sets/አሳ መቁጠር, ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀስ**

- ለልጅዎ **በዚህ ገጽ ላይ ስንት አሳዎች እንዳሉ ቁጠር** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግሞ አሳዎቹን ቀለም መቀባትና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ** ይበሉት። ልጅዎን እንደ አስፈላጊነቱ ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት።
- ከዚያ የተለያየ ብዛት ያላቸው አሳዎችን አንድ ላይ ያድርጉ፣ ምሳ፡ 3 አሳዎች ወይም 7 አሳዎች እና ልጅዎን እንዲቆጥራቸው ይጠይቁት። አሳዎቹን ከቆጠራቸው በኋላ በአጠቃላይ አሳዎቹ ስንት እንደሆኑ ይጠይቁት። ልጅዎ መልስ የማይሰጥዎ ወይም በድጋሚ መቁጠር የሚጀምር ከሆነ መጨረሻ የሚቆጥረው ቁጥር ድምራቸው እንደሆነ እንዲረዳ ለመርዳት ከቆጠረ በኋላ ድምሩን መልሰው ይንገሩት፣ ምሳ፡ **አዎ 3 አሳዎች አሉህ።**

## በግል መማር፡ የዳይኖሰር ግልገል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ቀለም ወይም ከለሮች፣ ግልገል መስሪያ ቁሳቁሶች፣ ምሳሌ፡ የወረቀት ጥቅሎች/ሶፍት፣ ያረጁ ካልሲዎች፣ የቡናማ ወረቀት ቦርሳዎች፣ ማጣበቂያ፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - ጥምዝ አይኖች ወይም የሰውነት ቆዳ መስሪያ ክር***

- ከልጅዎ ጋር ስለሚወዳቸው የተለያዩ አይነት ዳይኖሰሮች ተነጋገሩ። **የዳይኖሰር ግልገል መስራት ትችላለህ። ምን አይነት ዳይኖሰር ትሰራለህ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ትክክለኛ ወይም የፈጠራ ዳይኖሰር ሊሰራ ይችላል።
- ልጅዎ የዳይኖሰር ግልገሉን እንዲሰራ ይፍቀዱለት። የወረቀት ጥቅሉን ሊያስውብ ወይም የቡናማ ወረቀት ቦርሳዎቹን እጆቹን በመክተት ከታች እንደ ዳይኖሰር ግልገል አፍ አድርጎ መጠቀም ይችላል።
- የዳይኖሰር ግልገሉን ዛሬ ወደ ኋላ ላይ ለሚሰራው የዳይኖሰር ግልገል ቲያትር ያስቀምጡት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እውቀት፥ ያንን ስሜት በስም መጥራት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [ስሜቶች](), መስታወት ወይም እራስን የሚያሳይ ስልክ**



- ለልጅዎ **አካላችን እና ፊታችን ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማን ሊያሳዩ ይችላሉ። እስኪ ስሜትን በስም የመጥራት ጌም እንጫወት። እኔ ስሜቱን አስመስዬ እተውናለሁ። አንተ ደግሞ ስሜቱ ምን እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ጌሙን ከሚከተሉት መካከል ከ2-3 ስሜቶችን በመጠቀም ተጫወቱ፥
  - መናደድ፣ መበሳጨት፣ ማዘን፣ መደሰት፣ መገረም፣ መስጋት
- ልጅዎን ያ ስሜት ሲሰማው ምን እንደሚመስል ይጠይቁት። ልጅዎ ሰዎች እንዴት እራሳቸውን በተለያዩ መንገዶች ሊገልጹ እንደሚችሉ እንዲረዳ ለመርዳት መስታወት ይመልከቱ እና የእርስዎን አገላለጽ ከልጅዎ ጋር ያነጻጽሩ።
- ልጅዎ የተወሰኑ ስሜቶችን መተወን እንዲችል ሚናዎቻችሁን ተቀያየሩ።
- በተጨማሪም የሁኔታዎችን ምሳሌዎች ሊሰጡት እና ሁለታችሁም በዛ ሁኔታ ምን ስሜት እንደሚሰማችሁ ልታሳዩ ትችላላችሁ።

## ያንብቡ፥ ኤ ሪፍ ቴል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*A Reef Tale*]()




ኤ ሪፍ ቴል

- ከጀልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *A Reef Tale* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም **በባህር ውስጥ መኖር ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ በቀለጠ ድንጋይ ላይ አትዝለል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ማጣበቂያ፣ ወረቀት፣ ወረቀት ላይ ከ3-5 ቁጥሮችን ይጻፉ (የእያንዳንዱ ቢያንስ 2 ብዛት)**


- ቁጥሮቹ እንደ አለቶች ሆነው ያገለግላሉ። ቁጥሮቹን በደፈናው ወለል ላይ ያጣብቋቸው።
- ለልጅዎ **እስኪ ወለሉ በቮልካኖ ምክንያት በቀለጠ ድንጋይ እንደተሞላ አድርገን እናስብ። በቀለጠው ድንጋይ ላይ መሄድ ስለማንፈልግ ከአንድ አለት ወደ ሌላ አለት እንዘላለን። ቁም ብዬ ስነግርህ ባለንበት መቆም እና በአለቱ ላይ ያለውን ቁጥር መጥራት አለብህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ እርስዎን ቁም እንዲልዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።
- ይህን ተግባር የበለጠ ፈታኝ ለማድረግ ተጨማሪ ቁጥሮች ያስገቡ።

## በጋራ መማር፥ የዳይኖሰር ግልገል ቲያትር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ቀደም ሲል የተሰራው የዳይኖሰር ግልገል፣** ***በአማራጭነት - እንደ ቅጠሎችና የዛፍ ቅርንጫፎች ያሉ ሌሎች ደጋፊዎች፣ ዋሻዎችን የሚወክሉ ሳጥኖች፣ ወዘተ***

- ለልጅዎ **እስኪ የዳይኖሰር ግልገልህን በመጠቀም እንጫወት! ምን መተወን አለብን?** ይበሉት።
- አብራችሁ በምትጫወቱበትና የተለያዩ የዳይኖሰር ትዕይንቶችን በምትተውኑበት ወቅት ልጅዎን እንዲመራ ይፍቀዱለት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ቀን 19

## **STEM:** የዳይኖሰር ቅሪት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [Dinosaur Skeleton/ የዳይኖሰር ቅሪት](), ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ የጥጥ መወልወያዎች፣ የጥርስ ቆሻሻ ማውጫዎች፣ ትናንሽ መምጠጫዎች፣ ወዘተ**



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስዕሎቹን በመጠቀም ስለ ዳይኖሰር ቅሪቶች ተነጋገሩ። **ዳይኖሰሮች ከምድረ ገጽ የጠፉ ወይም በአሁኑ ወቅት የሌሉ ቢሆንም ከቅሪቶቻቸው ወይም አጥንቶቻቸው ብዙ ነገሮችን መማር እንችላለን** ይበሉት።
- **እነዚህን ነገሮች በመጠቀም የዳይኖሰር ቅሪት መስራት ትችላለህ** ይበሉት። መወልወያዎቹን እንዴት ወረቀቱ ላይ ማጣበቅ እንደሚችል ሞዴል ሊሰጡት ይችላሉ።
- ልጅዎ የጥጥ መወልወያዎቹን በቀጥታ በስዕሎቹ ላይ ሊያጣብቅ ወይም መወልወያዎቹን ወረቀት ላይ በማጣበቅ የራሱን ዳይኖሰር ሊሰራ ይችላል።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ዳይኖሰርህ ንገረኝ! ቅሪታቸው እንዴት ለመንቀሳቀስ ይረዳቸዋል?** ብለው ይጠይቁት።


## በግል መማር፡ ምን ይሰማቸዋል?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [*A Reef Tale*](), ወረቀት፣ ከለሮች**

ኩዩን አንድ ሃሳብ ነበራት።
“ኦህ፣ ኦህ! እኔ አይን
አንተ ደግሞ ጭንቅላት
መሆን እንችላለን።
አንዳችን ሌላችንን
መከላከል እንችላለን”

አልፊ ስለዚህ ነገር
አሰበበት። “እና ጓደኛዬ
ትሆኛለሽ ማለት ነው?”

ኩዩን ጭንቅላቷን በአዎንታ
በጣም ስለነቀነቀች፣
እንቅልፍ እንቅልፍ አላት።




- ለልጅዎ *A Reef Tale*ን ገጽ 26-27 ያሳዩት። ከዚያም **አልፊና ኩዩንን ተመልከት። ምን ስሜት እየተሰማቸው ነው ብለህ ታስባለህ? እንዴት መናገር ትችላለህ? አዎ፡ ደስተኛ ይመስላሉ፣ ፈገግታ ይታይባቸዋል** ይበሉት።
- **ደስተኛ ስለነበርክበት ጊዜ ልትስልና ልትስፍ ትችላለህ** ይበሉት። ልጅዎን ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ የደስታ ስሜት ስለተሰማህ ጊዜ ንገረኝ። ደስታ ሲሰማህ ሰውነትህ ምን አይነት ስሜት ይፈጠርበታል?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሃሙስ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ቀን 19

## እውቀት፥ ኤ ሪፍ ቴልን መልሶ መናገር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *A Reef Tale*

- ለልጅዎ **ይህን መጻፍ ትናንትና አንብበናል። በታሪኩ ውስጥ ስለተከሰቱ ስለ ሁለት ነገሮች ልትነግረኝ ትችላለህ? በመጀመሪያ ምን ተከሰተ? ቀጥሎስ ምን ተፈጠረ?** ይበሉት።
- ልጅዎ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ ምን እንደተከሰተ በሚመለከቱበት ወቅት ስዕሎቹን ይጠቀሙ። ከዚያም ልጅዎን የሚያስታውሳቸውን ሁለት ነገሮች እንዲነግርዎ ይጠይቁት።




ኤ ሪፍ ቴል

## የጆርናል ሙከራ፥ ኩዱን እና አልፊ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የኩዱን እና አልፊ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንዴት ጓደኞቻቸውን መርዳት እንደሚችሉ ተነጋገሩ፣ ምሳ፡ በሚያዝኑበት ወቅት ስሜታቸውን መጋራት ወይም የሚያጽናኑ ቃላት መንገር
- ልጅዎን ስለዚህ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ጓደኞችህን እንዴት እንደምትረዳቸው ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


ስም፥ ________________

ኩዱን እና አልፊ ጓደኛሞች ስለነበሩ እርስ በእርስ ይረዳዱ ነበር። እናንተ ጓደኞቻችሁን የምትረዱት እንዴት ነው?

**PK3 ስለ ዳይኖሰሮችና ቅሪት አካሎች በተመለከተ**

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ኩዪን እና አልፊ ጓደኛሞች ስለነበሩ እርስ በእርስ ይረዳዱ ነበር። እናንተ ጓደኞቻችሁን የምትረዱት እንዴት ነው?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ቀን 20

## STEM: የአቅጣጫ ቃላት ምርመራ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የእቃ መያዣ፣ በእቃ መያዣው ውስጥ የሚያዝ የቤት ውስጥ ቁስ**

- ለልጅዎ **እስኪ ጌም እንጫወት። እኔ አንተ የምትከተላቸውን መመሪያዎች እሰጥሀለሁ** ብለው ይንገሩት።
- አጠገብ፣ በመካከል፣ ከላይ፣ ከታች እና ቀጥሎ የሚሉትን ቃላት በመጠቀም መመሪያዎች ይስጡት። ለምሳሌ፡ ማንኪያውን ከሳጥኑ አጠገብ አስቀምጠው፣ እጅህን በእቃ መያዣውና ማንኪያው መካከል አድርግ፣ እጅህን ከራስህ በላይ አድርግ፣ እጅህን ከአገጭህ ስር አድርግ፣ ማንኪያውን ከሳጥኑ በታች አስቀምጥ፣ ወዘተ
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያ መስጠት እንዲችል ሚናዎቻችሁን ተቀያየሩ።

## በግል መማር፡ “ስለ ዳይኖሰርና ቅሪቶች”ን መሰናበት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ስለ ቅሪቶችና ዳይኖሰሮች ስንማር ቆይተናል** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር ስለ ቅሪቶችና ዳይኖሰሮች ትምህርት ውስጥ ስለወደደው ክፍል ተነጋገሩ። ይህ የወደደው ተግባር ወይም መጽሀፍ ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎን ከዚህ ክፍል ስለወደደው ነገር እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **የጻፍከው ስለ ምንድን ነው? ይህን የወደድከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 8 ሳምንት 4 ቀን 20

## እውቀት፥ ከጓደኞቼ ጋር የማደርጋቸው ነገሮች


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች ወይም ውሀማ ቀለም ጥቅል**

- ልጅዎን **ከጓደኞችህ ጋር ሆነህ ምን ማድረግ ትወዳለህ?** አንድ ላይ ማድረግ ስለሚችላቸው ስለተለያዩ ነገሮች ተነጋገሩ፣ ምሳሌ፡ መጫወት፣ መብላት፣ መደነስ፣ አንድ ላይ ሆኖ በአካል ወይም በኦንላይን መዝፈን፣ ወዘተ
- ከዚያም ልጅዎ ከጓደኞቹ ጋር ወይም ከአንድ የልብ ጓደኛው ጋር ሆኖ ማድረግ ስለሚፈልገው ነገር ስዕል እንዲስል ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።
- በተጨማሪም የሰዎችን ቅርጾች ቆርጦ በማውጣት እና በመቅረጫ ዱላዎች ወይም ዱላዎች ላይ በማጣበቅ ቀላል ግልገሎችን እንዲሰራ ሊጠይቁት ይችላሉ። ከዚያም ከጓደኞች ጋር ማድረግ ስለምትፈልጉት ነገር አስመስላችሁ በምትተውኑበት ወቅት አንድ ላይ ተጫወቱ።

## ያንብቡ፥ ኤ ሪፍ ቴል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*A Reef Tale/ኤ ሪፍ ቴል*]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው*A Reef Tale* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም **ኩዱንና አልፊ ጊዜያቸውን አንድ ላይ ማሳለፍ ይወዳሉ። ከአንተ ጋር አብሮ ጊዜውን እንዲያሳልፍ የምትፈልገው ሰው ማን ነው? አንድ ላይ ሆናችሁ ምን ታደርጋላችሁ?** ብለው ይጠይቁት



ኤ ሪፍ ቴል


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ወደ ክፍል 8 እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 8 ስር ልጅዎ ስለ ዳይኖሰሮች እና ነገሮች በጊዜ ሂደት እንዴት እንደሚቀየሩ ይማራል።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።